# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ | 81ኛ ዓመት ቁጥር 223 ሚያዝያ 13 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፦ 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


# ‹‹ጠዋት ጠዋት አክቲቪስት፣ ማታ ማታ ደግሞ ፖለቲከኛ መሆን አይቻልም››

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፦ ጠዋት ጠዋት አክቲቪስት፣ ማታ ማታ ደግሞ ፖለቲከኛ መሆን አይቻልም ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትርና የብልጽግና ፓርቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ።

«አዲስ ፖለቲካዊ እይታ-አዲስ ሀገራዊ እመርታ» በሚል መሪ ሐሳብ ለፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት በሰጡት ሥልጠና እንደገለጹት፤ ጠዋት ጠዋት አክቲቪስት፣ ማታ ማታ ደግሞ ፖለቲከኛ መሆን አይቻልም።፤ አሰራሩ በመቀላቀሉም በዴሞክራሲ ጉዞ ሂደት ላይ እንቅፋት ፈጥሯል ።

አክቲቪስትና ፖለቲከኛ፣ አክቲቪስትና ምሁርነት በመቀላቀላቸው በሃሳብ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን የዴሞክራሲ ጉዟችንን ችግር መፍጠሩን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ይህ መቀላቀልም በሃሳብ ፋክክራችን ውስጥ እንቅፋት የፈጠሩና የጎዱን በመሆናቸው ጠዋት ጠዋት አክቲቪስት፣ ማታ ማታ ደግሞ ፖለቲከኛ መሆን አይቻልም ብለዋል።



አክቲቪስት በሆነ ጉዳይ ላይ አነቃቂ ነው። በጤና፣ በመብት ጉዳይ ላይ የሚያነቃ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በኢትዮጵያ ግን ጠዋት ጠዋት አክቲቪስት መሆን፣ ማታ ማታ ደግሞ ፖለቲከኛ በመሆን አሰራሩ መቀላቀሉንና ችግርም እየፈጠረ መሆኑንም አመልክተዋል።

ከተመረጠ የብልጽግና አባል ይሆናል፣ ካልተመረጠ ደግሞ በዩቲዩቡ ይጮሃል ይህ መታረም እንደሚገባው ነው የተናገሩት።

አክቲቪስትና ፖለቲካ ተቋም ውስጥ መስራት ለየቅል ናቸው ያሉት ዶክተር ዐቢይ፤ አክቲቪዝም ተጠያቂነት የለውም። የፖለቲካ ሰዎች ስንሆን ግን መናገር

“ጠዋት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ወደ ውጭ በሚላኩት አትክልትና ፍራፍሬ ላይ የተደረገው የዋጋ ማሻሻያ ተግባራዊ ሲደረግ ነው

**-ማሻሻያው ተግባራዊ እንዲደረግ በብሄራዊ ባንክ በኩል ለሁሉም ባንኮች ሰርኩላር ተላልፏል**

**ግርማቸው ጋሻው**

አዲስ አበባ፡- ወደ አጎራባች አገሮች በሚላኩት የአትክልትና ፍራፍሬ ዋጋ ላይ በቅርቡ የተደረገው ማሻሻያ የተቀመጠለት የሽግግር ጊዜ እንደተጠናቀቀ ተግባራዊ እንደሚደረግ የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ዘርፍ የኤክስፖርት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክተር አቶ መኮንን ሰሎሞን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ወደ አጎራባች አገሮች በሚላኩት የአትክልትና ፍራፍሬ ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ የተተመነው ከ50 ዓመታት በፊት ቢሆንም እስካሁን ድረስ ምንም ዓይነት ማሻሻያ ሳይደረግበት ቆይቷል።በቅርቡ በእነዚህ ምርቶች ላይ የተደረገው የዋጋ ማሻሻያም ተመንም የሽግግር ጊዜው እንዳበቃ ተግባራዊ ይደረጋል። ለዚህም በብሄራዊ ባንክ በኩል ለሁሉም ባንኮች ሰርኩላር

ወደ ውጭ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ለፋሲካ በዓል በቂ የምርት አቅርቦት ዝግጅት ማድረጉን ኤጀንሲው አስታወቀ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ለመጪው የፋሲካ በዓል በቂ የምርት አቅርቦት ዝግጅት ማድረጉን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሕብረት ሥራ ኤጀንሲ አስታወቀ፡፡

የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ግዛቸው አሊ፤ በዓላት ሲመጡ በኤጀንሲው አማካኝነት ዝግጅት ተደርጎ በእቅድ እንደሚመራ፤ በዚሁ መሠረት ኤጀንሲው ከወር በፊት ፕሮግራም ይዞ መዘጋጀቱንና በየደረጃው ላሉ ማህበራት ገለጻ የመስጠት ሥራ መከናወኑን እንዲሁም የሥራ ክፍፍል ማድረጉን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገልጸዋል፡፡

ለፋሲካ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ሰሞኑን በክልሉ የታየው የሰላም መደፍረስ ዋነኛ ዓላማው ሕዝብን ከሕዝብ ለማጋጨት ያለመ ነው

የአማራ ክልል መንግሥት

- **በሰሜን ሸዋ እና በኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞኖች ተከስቶ የነበረው ግጭት ተረጋግቷል**

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- ሰሞኑን በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ እና ኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞኖች በአንዳንድ አካባቢዎች ተከስቶ የነበረው ግጭት ዋነኛ ዓላማው ሕዝብን ከሕዝብ የማጋጨት መሆኑን የክልሉ መንግሥት ገለጸ፡፡ ተከስቶ የነበረው ግጭት የጸጥታ አካላት እና ሕብረተሰቡ በጋራ ባደረጉት ጥረት እና ርብርብ መረጋጋቱ ተጠቆመ፡፡

የክልሉ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ግዛቸው ሙሉነህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሰሞኑን በኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር እና ሰሜን ሸዋ ዞን በተለይ ኤፍራታና ግድም አንድ ወረዳ ሞላሌ በምትባል አንድ መንደር እና ሸዋሮቢት ጀጀባ የሚባል ቀበሌ ላይ እንዲሁም ሁለቱ ዞኖች የሚዋሰኑባቸው የጅሌጥሙጋ ወረዳ አካባቢ ግጭት ተከስቶ ነበር፡፡ በግጭቱ የሰው ህይወት ማለፉንም ገልጸዋል፡፡

አካባቢው ኦነግ ሸኔ የሚንቀሳቀስበት መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የግጭቱ ጠንሳሾች ጸረ ሕዝቦች የሆኑና ዋነኛ አላማቸውም ሕዝብን ከሕዝብ ማጋጨት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ግጭቱን የብሔር ግጭት ለማድረግም በከፍተኛ ሁኔታ ተሰርቶ እንደነበር አክለው ገልጸዋል፡፡

የአማራ ልዩ ኃይል፣ ፖሊስ እና የፌዴራል ፖሊስ



ሰሞኑን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







ዜና

# "የአፍሪካ አገራት ደመናን የማበልጸግ ቴክኖሎጂን ከኢትዮጵያ ሊማሩ ይገባል"

- ዶክተር አሞስ ማካራው

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ አገራት ደመና የማበልጸግ ቴክኖሎጂን በዘርፉ ውጤታማነቷን ካሳየችው ኢትዮጵያ ሊማሩ ይገባል ሲሉ በዓለም የሜቲዮሮሎጂካል ተቋም የአፍሪካ አህጉራዊ ጽህፈት ቤት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አሞስ ማካራው ተናገሩ።

በዓለም የሜቲዮሮሎጂ ተቋም አህጉራዊው ማህበር አንድ (RA 1) የማኔጅመንት ቡድን ለሁለት ቀናት የሚቆየውን ስብሰባ ትናንት በአዲስ አበባ ጀምሯል። በወቅቱ ዶክተር አሞስ ማካራው እንዳስታወቁት፤ ኢትዮጵያ ደመናን በማበልጸግ ቴክኖሎጂን ለመጠቀም የምታደርገው ጥረት የሚደነቅ ነው። ከዚህ ሳይንሳዊ ሥራ በርካታ የአፍሪካ አገራት ልምድ መቅሰም ይኖርባቸዋል።

ደመናን በማበልጸግ (Cloud Seeding) ቴክኖሎጂ ኢትዮጵያ እየሄደችበት ያለው ርቀት ውጤታማ አድርጓታል ያሉት ዶክተር አሞስ፤ የዚህ አይነቱ ቴክኖሎጂ ትግበራ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያደርሰውን የድርቅ አደጋ ለመቋቋም አንዱ አማራጭ መሆኑን ተናግረዋል።

በተለይም ተፈጥሯዊ ዳመናን ወደ ዝናብ በመቀየርም ሆነ ሰው ሰራሽ ደመናን በማበልጸግ የሚከናወነው ተግባር በድርቅ ለሚጎዱ የአፍሪካ አገራት ተጨማሪ የውሃ አማራጭ እንዲያገኙ ይረዳል ብለዋል።



በአፍሪካ ያሉ ወደብ አልባ አገራት ቴክኖሎጂውን በይበልጥ መጠቀም እንዳለባቸው የጠቆሙት ዶክተር አሞስ፤ እነዚህ የአፍሪካ አገራት በተለይ ከአየር ንብረት መለዋወጥ ጋር ተያይዞ በሚከሰት ተደጋጋሚ ድርቅ ይጠቃሉ። አገራቱ ደግሞ ከውቅያኖሶች ያላቸው ርቀት ረጅም በመሆኑ የውቅያኖሱን ውሃ በማጣራት በድርቅ ለተጎዱ አካባቢዎች የሚያውሉበት አማራጭ እንደሌላቸው ገልጸዋል።

ደመናን የማበልጸግ ቴክኖሎጂን ተግባራዊ በማድረግ በሰው ሰራሽ መንገድ የሚገኘውን የዝናብ ውሃ ተጠቅመው በድርቅና የተለያዩ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸውን ችግሮች ለመቅረፍ ጥረት ማድረግ እንደሚኖርባቸው ተናግረዋል።

የአፍሪካ አገራት በየዓመቱ ከሚያገኙት ተፈጥሯዊ ዝናብ ባለፈ ቴክኖሎጂውን ተጠቅመው ተጨማሪ የዝናብ ውሃን መሰብሰብ ይችላሉ። በዚህም ለግብርና ሥራም ሆነ ለተለያዩ አገልግሎቶች መጠቀም የሚችሉበት ዕድል ቀርቦላቸዋል ብለዋል።

ከዚህ ባለፈ የአፍሪካ አገራት በዝናብ ዕጥረት ምክንያት የሚደርስባቸውን የግድቦች ውሃ መጠን መቀነስና ተያያዥ ችግሮችን ለመፍታትም ዳመናን የማበልጸግ ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ጠቁመዋል።

በዚህ ረገድ ደግሞ ኢትዮጵያ የተሻለ ልምድና ውጤት ማግኘቷን በተግባር አሳይታለች ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ልምዱን መቅሰም የሚፈልጉ ታዳጊ የአፍሪካ አገራትን ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የተለያዩ ስልጠናዎችን መውሰድ ይገባቸዋል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ቴክኖሎጂውን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ የኢትዮጵያ መንግሥት እያሳየ ያለው ጥረት የሚደነቅ ነው ያሉት ዶክተር አሞስ፤ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ለጉዳዩ የሰጡት ትኩረትም ለሌሎችም አገራት ተሞክሮ መሆን የሚችል ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ከደመናን ማበልጸግ በተጨማሪ ለሜቲዮሮሎጂ አገልግሎት የሚታገዝ ሳተላይት ማምጠቅ መቻሉ ለኢትዮጵያ ትልቅ ስኬት መሆኑን የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፤ ይህን አይነት ልምድ ሌሎች አገራትም ሊከተሉት ይገባል ብለዋል።

አፍሪካውያን ችግሮቻችንን ተረዳድተን ማለፍ ይጠበቅብናል፤ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያም ቴክኖሎጂውን ለመቅሰም የሚፈልጉ አገራት ሲገኙ ትብብር ማድረግ ይኖርባታል ብለዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ድርቅ በሚከሰትባቸው ስፍራዎች ደመናን በማበልጸግ ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ እንዴት የዝናብ ውሃ ማግኘት ይቻላል? በሚሉና ተያያዥ ቴክኒካዊ ጉዳዮች ላይ የእርስ በርስ ድጋፍ በመሰጣጣት የአፍሪካ አገራት በጋራ መስራት ይኖርባቸዋል።

ኢትዮጵያ የደመና ማበልጸግ ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ለማዋል በምታከናውነው ተግባር ድሮኖችን ጥቅም ላይ እያዋለች እንደሚገኝ ታውቋል።

# በበዓላት ወቅት የኃይል መቆራረጥ እንዳያጋጥም እየሠራ መሆኑን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በቅርቡ በሚከበሩት የትንሳኤና የኢድ አልፈጥር በዓላት ወቅት የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ እንዳያጋጥም ቅድመ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ፡፡

የአገልግሎቱ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ መላኩ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በበዓላት ወቅት የህብረተሰቡ የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላጎት ከወትሮው በተለየ ይጨምራል፡፡ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የትንሳኤና የኢድ-አልፈጥር በዓላት መቃረባቸውን ተከትሎ ሊኖር የሚችለውን የኃይል መቆራረጥ ችግር ለመፍታት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በማከናወን ላይ ይገኛል ብለዋል፡፡

ተቋሙ በበዓላቱ ዋዜማና በበዓላቱ ዕለት የኤሌክትሪክ ኃይል ሳይቆራረጥና ሳይዋዥቅ ለህብረተሰቡ ለማቅረብ አስቀድሞ የቅድመ መከላከል ሥራዎች እየተሠሩ ነው ያሉት አቶ መላኩ፤ ችግሩ ከተከሰተም አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የአስቸኳይ ጥገና ግብረ ኃይል አዋቅሮ ወደ ሥራ ገብቷል፡፡ በተለይም ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ የኃይል መቆራረጥ የሚስተዋልባቸውን አካባቢዎች በመለየት በመካከለኛና በዝቅተኛ መስመሮች ላይ ጭነት የማመጣጠንና የቅድመ መከላከል ጥገና ሥራዎች በመሥራት ላይ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

ከኃይል ማመንጫ ጀምሮ እስከ ማሰራጫ መስመሮች ድረስ ብልሽቶች ሲያጋጥሙ በአፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎትና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በጋራ በመሆን ጥምር ግብረ ኃይል በማቋቋም ወደ ሥራ መግባታቸውንም አቶ መላኩ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ደንበኞችም በቤት ውስጥ የሚገለገሉባቸውን የኤሌክትሪክ ቁሳቁሶች ኃይል ቆጣቢ እንዲሆኑ ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው አስታውሰው፤ አጠቃቀማቸውም ለአደጋ እንዳያጋልጥ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡ ፡ የኤሌክትሪክ ኃይል ጭነት በማይበዛበት ሰዓታት



በተለይም ከምሽቱ 4፡00 እስከ ንጋቱ 11፡00 ባሉት ጊዜያት በመጠቀም የተሻለ የኤሌክትሪክ ኃይል ከማግኘት ባለፈ የኤሌክትሪክ መቆራረጥንም ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው አስረድተዋል፡፡

የኤሌክትሪክ ኃይል በሚቋረጥበት ጊዜ የጥገና ሥራ ለማከናወን የተቋማችንን መታወቂያ የያዙ የቴክኒክ ባለሙያዎቻችን በተለያዩ አካባቢዎች ለሥራ ጉዳይ እንደሚንቀሳቀሱ ህብረተሰቡ ተገንዝቦ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ ይኖርበታል ያሉት አቶ መላኩ፤ የቅድመ ክፍያ ቆጣሪ ተጠቃሚ ደንበኞችም ያስሞሉት ኃይል ማለቅና አለማለቁን በማረጋገጥ በዓሉ ከመድረሱ በፊት ካርዳቸውን እንዲሞሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

ይሁንና የተቋሙ የጥገና ሰራተኞች በመምሰል መሠረተ ልማቱ ላይ ስርቆትና ጉዳት ሊያደርሱ እንደሚችሉ ጠቁመው፤ ህብረተሰቡ የኤሌክትሪክ ማሰራጫ መስመሮችን በመጠበቅ እንዲተባበርና መሰል እኩይ ተግባር የሚፈፅም አካል ሲመለከት ለሚመለከታቸው የሕግ አካላትና ለተቋሙ ማሳወቅ ይገባዋል ብለዋል፡፡

የቱን ያህል የቅድመ ዝግጅት ሥራ ቢሠራ መቆራረጡን ዜሮ ማድረግ አይቻልም ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ህብረተሰቡ የኃይል መቆራረጥ ሲያጋጥም በ905 ነጻ የጥሪ ማዕከል በማሳወቅ አፋጣኝ የጥገና አገልግሎት ማግኘት እንደሚችል አስገንዝበዋል፡፡

# የኦዲት ግኝት የተመዘገበባቸው 39 የፌዴራል ባለበጀት ተቋማት አመራሮች በገንዘብ እንዲቀጡ ተወሰነ

አዲስ አበባ፡- የኦዲት ግኝት የተመዘገበባቸው 39 የፌዴራል ባለበጀት መስሪያ ቤቶች አመራሮች በገንዘብ እንዲቀጡና የጽሁፍ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንዲጻፍባቸው መወሰኑን የገንዘብ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በዋና ኦዲተር ባለፉት ሶስት ዓመታት ተመርምረው የኦዲት ግኝት የተመዘገበባቸው ዘጠኝ የፌዴራል ባለበጀት መስሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎችና የፋይናንስ ዳይሬክተሮች እያንዳንዳቸው በቅደም ተከተል 10ሺ እና 9ሺ ብር እንዲቀጡ የተወሰነባቸው ሲሆን በሌሎች 30 ባለበጀት መስሪያ ቤቶች ላይ ደግሞ ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንዲጻፍባቸው ተወስኖ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

የገንዘብ ቅጣቱ የተወሰነባቸው የአሶሳ፣ የቡሌ ሆራ፣ የደብረማርቆስ፣ የኦዳ ቡልቱ፣ የባህር ዳር፣ የሲቪል ሰርቪስ፣ የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲዎች ፕሬዚዳንቶችና የፋይናንስ ዳይሬክተሮች ሲሆን የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽንና የኢትዮጵያ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የበላይ ኃላፊዎችና የፋይናንስ ዳይሬክተሮችም የገንዘብ ቅጣቱ ከተወሰነባቸው ተቋማት መካከል ይገኙበታል፡፡

ከ2010 እስከ 2012 ዓ.ም ባሉት ሶስት ዓመታት ውስጥ ሂሳባቸው የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ የእነዚህ 39 የፌዴራል ባለበጀት መስሪ ቤቶች ኃላፊዎችና ተቋማት ላይ እርምጃ የተወሰደው "የፋይናንስ ኃላፊነትን በአግባቡ ባለመወጣት የሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች መመሪያ ቁጥር 48/2009» መሰረት መሆኑንም ገልጸዋል።

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15.1 መሰረት በማንኛውም የመንግሥት መስሪያ ቤት የተሾመ ወይም የተመደበ ሰው በመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፤ በአዋጁ መሰረት በወጡት ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት በህግ የተወሰነውን ኃላፊነትን ባለመወጣቱ ምክንያት በዚህ መመሪያ ከሶስት ጊዜ በላይ ቅጣት ከተጣለበት ከኃላፊነት እንዲነሳ ሊደረግ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

የገንዘብ ቅጣት ከተላለፈባቸው ዘጠኝ የፌዴራል ባለበጀት መስሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎችና የፋይናንስ ዳይሬክተሮች ውስጥ ሰባቱ የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንቶችና የፋይናንስ ዳይሬክተሮች ሲሆኑ ሁለቱ ደግሞ የሌላ ባለበጀት መስሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎችና የፋይናንስ ዳይሬክተሮች መሆናቸውን የገንዘብ ሚኒስቴር አስታውቋል።

ዜና

# የፋሲካ በዓል የገበያ ዋጋ በአዲስ አበባ

**መላኩ ኤርሴ**





የፋሲካ በዓል ገበያ የተለያዩ የአዲስ አበባ ቦታዎች አንዳንድ ምርቶች ዋጋ ላይ መጠነኛ ጭማሪ ይታያል።በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ምርቶች ዋጋ ላይ ይህ ነው የሚባል ጭማሪ እንዳልታየ ሸማቾች ነግረውናል። ወይዘሮ ሶስና ሙሉጌታ በሾላ ገበያ ለበዓሉ ማክበሪያ የሚሆኑ ምርቶችን ሲገዙ ካገኘናቸው ሸማቾች አንዱ ናቸው።

ወይዘሮዋን ዶሮና እንቁላል ሲገዙ ነው ያገኘናቸው። ዘንድሮ የዶሮ ዋጋ ካሰቡት በላይ ጭማሪ አሳይቷል ይላሉ። ከቤታቸው ወደ ገበያ ሲወጡ አንድ ዶሮ ከ400 እስከ 500 ብር ለመግዛት አስበው ቢሆንም፤ ገበያ ሲደርሱ ዶሮ ባሰቡት ዋጋ ማግኘት እንዳልቻሉ ነግረውናል።

ሀገሪቷ ካለችበት ነባራዊ ሁኔታ አንጻር የምርቶች ዋጋ ሊጨምር እንደሚችል አስበው የነበረ ቢሆንም፤ በዶሮ ላይ የታየው የዋጋ ጭማሪ አይነት ያጋጥማል ብለው አልጠበቁም። መካከለኛ ዶሮ ከ700 እስከ 800 ብር እየተሸጠ ነው። በገበያው ውስጥ ዶሮ በብዛት ቢኖርም ዋጋው እንዲህ የተወደደበት ምክንያት እንዳልገባቸው ገልጸዋል።

በውድ ዋጋም ቢሆን መካከለኛ ዶሮ ገዝተዋል። ዶሮ ያለ ሽንኩርት መስራት እንደማይታሰብ የጠቆሙት ወይዘሮ ሶስና፤ የሽንኩርት ዋጋ ላይም መጠነኛ ጭማሪ መታየቱን ጠቁመዋል። ከበዓሉ ቀደም ብሎ በ25 ብር ሲሸጥ የነበረው ሽንኩርት አሁን በ35 ብር እየተሸጠ መሆኑን ነግረውናል።

አቶ ኃይሉ ያደታ የዶሮ ነጋዴ ናቸው። በዓላት በሚደርሱበት ወቅት ከተለያዩ ክልሎች ዶሮዎችን እያመጡ በሾላ ገበያ ይሸጣሉ። ዘንድሮ ከአርሲ አካባቢ 120 መካከለኛ ዶሮዎችን ከ700 እስከ 750 ብር ገዝተው እንዳመጡ የሚናገሩት አቶ ኃይሉ፤ ከ750 እስከ 800 ብር ለመሸጥ ማቀዳቸውን ተናግረዋል።

ከአምናው ፋሲካ አንጻርም ሲታይ በዶሮ ዋጋ ላይ የተጋነነ ጭማሪ እንደሌለ የሚናገሩት አቶ ኃይሉ፤ ባለፈው ዓመት ከ600 እስከ 650 ብር ከክልሎች በማምጣት ከ700 እስከ 750 ብር መሸጣቸውን ያስታውሳሉ።

ባለፈው ዓመት ለንግድ ያመጡትን ዶሮዎችን በጥቂት ቀናት ውስጥ ጨርሰው መመለሳቸውን የሚናገሩት አቶ ኃይሉ፤ ዘንድሮ ግን ብዙም ዶሮ የሚገዛ ሰው አለመኖሩን አንስተዋል። ያመጧቸው ዶሮዎች ገዥ አጣ ይሆን የሚል ስጋት ፈጥሮብኛል ብለዋል።

አቶ ብዙነህ ቡንጂ በካሳንቺስ ሸማቾች ማህበር እንቁላል ሲገዛ ነው ያገኘነው። በሱቆች የሚታየው የሸቀጦች ዋጋ ኪስ የሚፈትን መሆኑን ጠቁሞ፤ ሸማቾች ማህበር የሚሸጥበት ዋጋ የተሻለ ነው ብሏል። በሱቅ በ8 ብር እየተሸጠ ያለውን እንቁላል ከሸማቾች ማህበር በ7 ብር መግዛቱን ጠቁሞ፤ ከአምናው አንጻር ሲታይ ጭማሪ እንዳልታየበትም ነግሮናል።

በሸማቾች ማህበሩ መጋዘን ውስጥ ግን ሽንኩርት የመሳሰሉ ምርቶች እንደተራገፉ ወዲያው እያለቁ በመሆናቸው ሸማቾች በፈለጉበት ሰዓት ለማግኘት መቸገራቸውን ጠቁመዋል። መንግሥት ለሸማቾች ማህበራት ምርት በብዛት የሚቀርብበትን ሁኔታ ሊያመቻች እንደሚገባ ጠቁሟል።

ከፍተኛ የዋጋ ልዩነቶች ከሚስተዋልባቸው ምርቶች አንዱ ቅቤ ነው። ለጋ ቅቤ በሾላ ገበያ በ800 ብር እየተሸጠ ሲሆን፣ መካከለኛው ቅቤ ደግሞ በ700 እንዲሁም የቆየ በ600 ብር እየተሸጠ ነው። በሸማቾች ማህበራት ሱቆች ውስጥ ደግሞ በ310 ብር እየተሸጠ መሆኑን ባደረግነው የገበያ ቅኝት ማወቅ ችለናል።

ወይዘሮ ዘነበች ታደሰ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስምንት ከሚገኘው እድገት በህብረት የሸማቾች ማህበር ቅቤ እና ዱቄት ገዝተው ሲወጡ ነው ያገኘናቸው። ከኑሮ ውድነቱ የተነሳ እንደ እሳቸው ዝቅተኛ ገቢ ያለው ሰው ኑሮውን በአግባቡ ለመምራት ብሎም በዓላትን ለማክበር ፈታኝ እየሆነበት ቢመጣም በሸማቾች ማህበራት በኩል ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረቡ በመሆኑ የኑሮ ውድነቱን እንዲቋቋሙ እንዳስቻላቸው ተናግረዋል።

ቅቤ ኪሎ በ310 ብር ሂሳብ መግዛታቸውን የጠቆሙት ወይዘሮ ዘነበች፤ በሸማቾች ማህበራት ቅቤ እየተሸጠ ያለበት ዋጋ በገበያ ላይ ካለው ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ልዩነት መኖሩን አንስተዋል።የሸማቾች ማህበሩ ከእጥፍ በላይ ቅናሽ እንዳለው ጠቁመዋል።

በግለሰብ ሱቆች አንድ ኪሎ ቅቤ ከ600 እስከ 800 እየተሸጠ መሆኑን አስታውሰው የቅቤው ለጋነት ላይ ልዩነቶች ቢኖሩም በሸማቾች ማህበራት በተመጣጣኝ ዋጋ እየቀረበ መሆኑ አቅም ለሌላቸው ዜጎች እፎይታን የሚሰጥ ነው ብለዋል።

ወይዘሮ ዘነበች የዘይት እጥረት መኖሩን አንስተዋል። ዘይት በተመጣጣኝ ዋጋ እየቀረበ ቢሆንም በአካባቢው ከፍተኛ የዘይት ፈላጊ ማህበረሰብ በመኖሩ ዘይት ለመግዛት ያለው ሽሚያ እልህ አስጨራሽ መሆኑን አንስተዋል። ከሌሊት ጀምሮ ወረፋ ጠብቆ ዘይት መሸመት እንደእሳቸው ላሉ አቅመ ደካሞች ፈታኝ ነው ብለዋል።

ወይዘሮ ፋሲካ በቀለ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስምንት የእድገት በህብረት ሸማቾች ማህበር ውስጥ የሽያጭ ሰራተኛ ናቸው። ቅቤ፣ ሽንኩርት፣ ዘይት፣ ዱቄት፣ ስኳር፣ ጨምሮ የተለያዩ ምርቶች በማህበሩ መጋዘን ውስጥ መኖራቸውን አረጋግጠዋል።

ሽንኩርት ከበዓሉ ቀደም ብሎ በ25 ብር እየተሸጠ የነበረ ሲሆን አሁን ደግሞ በ36 ብር እየተሸጠ ነው። ቅቤ አምና በ250 ብር ሲሸጥ የነበረ ሲሆን ከበዓሉ ቀደም ብሎ በ270 ብር እየተሸጠ የነበረው ሰሞኑን ወደ 310 ከፍ ማለቱን ጠቁመዋል። በዋጋው ላይ መጠነኛ ጭማሪው የታየውም ምርቶቹን ማህበሩ ገዝቶ በሚያመጣበት ዋጋ ላይ ጭማሪ በመኖሩ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በአሁኑ ጊዜ ህዝቡ በዋናነት እየፈለገ ያለው ዘይት ለሸማቾች ማህበሩ በሚፈለገው መጠን ባለመቅረቡ ከህዝቡ ፍላጎት ጋር የሚጣጣም የዘይት አቅርቦት እስኪመጣ ድረስ ዘይት እየተሸጠ አለመሆኑን አንስተዋል። ተጨማሪ የዘይት ምርት እንደመጣም መሸጥ እንደሚጀመር አመልክተዋል።

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስምንት ከሳንቺስ የሸማቾች ማህበር የሰው ሃብት አስተዳደር ጎሳዬ ሻይ እንደተናገሩት፤ ማህበሩ የግብርና ምርቶችና የኢንዱስትሪ ውጤቶችን ነው ያቀረበው። ከኢንዱስትሪ ምርቶች ዘይትና ሳሙና ፣ ከግብርና ምርቶች ደግሞ እንቁላል፣ የመሳሰሉ ምርቶችን አቅርቧል።አንድ እንቁላል በ7 ብር እየተሸጠ ነው።አምስት ሌትር ፈሳሽ ዘይት በ850 ብር እየተሸጠ ነው። ይህም ከአምናው አንጻር ግማሽ ገደማ ልዩነት አለው።

ሌሎች ምርቶች ዋጋ ላይ ግን የተጋነነ ጭማሪ አይታይም የሚሉት አቶ ጎሳዬ ፤የሸማቾች ማህበሩ ሽንኩርት ከትናንት በስቲያ በ35 ብር ሲሸጥ የነበረ ሲሆን ሽንኩርት በማለቁ ተጨማሪ ሽንኩርት ከህብረት ሥራ ዩኒየኖች ለማስመጣት ጥረት እያደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጋዜጠኞች ቡድን በሾላ ገበያ፣ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስምንት የእድገት በህብረት ሸማቾች ህብረት ሥራ ማህበርና በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስምንት ካሳንቺስ ሸማቾች ማህበር የገበያ ቅኝት አድርጓል።በሾላ ገበያ ተዘዋውሮ እንደተመለከተው ነጋዴዎች በገበያ ስፍራዎች የተለያዩ ምርቶችን ይዘው ገዥዎችን እያስተናገዱ ቢገኙም ገበያው የተቀዛቀዘ መሆኑን ተመልክተናል።በገበያ ስፍራዎች ዶሮ፣ ቅቤ፣ እንቁላል፣ ሽንኩርት እና ሌሎች የግብርና ምርቶች ይታያሉ።

# ለመጪው የትንሳዔ በዓል 40 ሺህ የሚሆኑ የዳልጋ ከብቶች ለገበያ ይቀርባሉ

## * ቄራዎች ድርጅት ከ3 ሺህ በላይ የዳልጋ ከብቶች አርዶና በልቶ ለገበያ ለማቅረብ ዝግጅቱን አጠናቋል

**ውብሸት ሰንደቁ**



ከአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ ጋር ተባብረው በመሥራት አቅርቦቱ ሳይስተጓጎል እንዲካሄድ ስምምነት ላይ እንደደረሱ ወይዘሮ መዓዛ ተናግረዋል።

ደላሎች በመካከል ገብተው የዋጋ ንረት እንዳይፈጠር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ እየሠራን ነው ያሉት

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ለመጪው የትንሳዔ በዓል ከ30 ሺህ እስከ 40 ሺህ የሚሆኑ የዳልጋ ከብቶች ለገበያ ለማቅረብ ዝግጅቱን ማጠናቀቁን የኢትዮጵያ የቁም እንስሳት ነጋዴዎች ማኅበር አስታወቀ። ቄራዎች ድርጅት በበዓሉ ዕለት ከሶስት ሺህ በላይ የዳልጋ ከብቶች አርዶና በልቶ ለገበያ ለማቅረብ ዝግጅቱን ማጠናቀቁን አመልክቷል።

በትላንትናው ዕለት የኢትዮጵያ የቁም እንስሳት ነጋዴዎች ማኅበር፣ የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅትና የአዲስ አበባ ሉኳንዳ ነጋዴዎች ማኅበር በጋራ በመሆን መግለጫ ሰጥተዋል። በመግለጫው የኢትዮጵያ የቁም እንስሳት ነጋዴዎች ማኅበር ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሮ መዓዛ ቀለሙ እንዳስታወቁት፤ ለመጪው የትንሳዔ በዓል ከ30 ሺህ እስከ 40 ሺህ የሚሆኑ የዳልጋ ከብቶች ለገበያ እንዲቀርቡ ለማድረግ ዝግጅቱ ተጠናቋል።

ሥራ አስፈፃሚዋ እንዳሉት፤ የትንሳኤ በዓልን አስመልክቶ በአዲስ አበባ በሚገኙ አራት የቁም እንስሳት ገበያ ማዕከላትና በሌሎችም መገበያያ ሥፍራዎች ከ30 እስከ 40 ሺህ የሚሆኑ የዳልጋ ከብቶችን ወደ ከተማዋ ለማስገባት ዝግጅት ተደርጓል። ይህን ያህል የቁም እንስሳት መግባቱም ዋጋ እንዳይንር አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

የአቅርቦት እጥረት እንዳይኖር ከክልሎች ጋር ተነጋግረው እየሰሩ መሆኑንና የጭነት መኪና የሰዓት ገደቦች እንዲነሱ

ሥራ አስፈፃሚዋ፤ በቁም እንስሳት አቅርቦት በኩል እጥረት እንዳለ የሚያመላክቱ መረጃዎች ባለመኖራቸው የዋጋ ጭማሪ ይደረጋል የሚል ስጋት የለም ብለዋል።

የአዲስ አበባ ሉኳንዳ ነጋዴዎች ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ አየለ ሳህሌ በበኩላቸው ለትንሳዔ በዓል የሥጋ አቅርቦት የማኅበሩ አባላት ቅድመ ዝግጅታቸውን ማጠናቀቃቸውን ገልፀው፤ ከአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት ጋር በመሆን አገልግሎቱን ለማሳለጥ ዝግጅቶች መጠናቀቃቸውን ተናግረዋል።

የዳልጋ ከብት ግብይቱ ከትላንት ጀምሮ መጀመሩንና ኅብረተሰቡን በተመጣጣኝ ዋጋ ተጠቃሚ ለማድረግ እንደሚሠሩ ገልፀዋል።

አቶ አየለ፤ የሥጋ መሸጫ ዋጋን በተመለከተ ገበያው የሚወሰነው በሚኖረው የቁም እንስሳት ግብይትና አቅርቦት ነው፤ በአሁኑ ጊዜም የተጋነነ የዋጋ ጭማሪ ይኖራል የሚል ግምት የለኝም ሲሉ ተናግረዋል። ሥጋ ቤቶች ተጨማሪ ዕሴት ታክስ ከፋዮች መሆናቸውና የቁም እንስሳቱ አዋጭነት በግምት ላይ የተመሠረተ መሆኑ ዋጋውን አስቀድሞ ለመተንበይ ይከብዳል ሲሉም አብራርተዋል።

ሌላው መግለጫ የሰጡት የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሰኢድ እንድሪስም ለትንሳዔ በዓል የሥጋ አቅርቦት ቅድመ ዝግጅት ማጠናቀቃቸውን ገልፀው በዕለቱ ከሶስት ሺህ በላይ የዳልጋ ከብት አርዶና በልቶ ለገበያ ለማቅረብ ሥራዎች ተጠናቀዋል ብለዋል።

በተጨማሪም ከ4 ሺህ እስከ 5 ሺህ የሚሆኑ የበግና ፍየል ሥጋዎች በድርጅቱ ሥር በሚገኙ ሱቆች በበዓሉ ዕለት የሚቀርቡ መሆኑን ሥራ አስኪያጁ ገልፀዋል።

አቶ ሰኢድ እንዳሉት፤ የሥጋን ዋጋ ለማረጋጋት ሲባል በቄራ ሱቆች በሚሠሩ የሥጋ አቅራቢ ድርጅቶች የበሬ ሥጋ 350 ብር እንዲሁም የበግና የፍየል ሥጋ 260 ብር በኪሎ ቫትን ጨምሮ ይሸጣል። ይህ ዋጋ የተለየ ነገር እስካልተፈጠረ ድረስ ለሚቀጥለው አንድ ዓመት ይቆያል።

ከሕገ ወጥ ዕርድ ጋር በተያያዘ ያልተመረመሩ እንስሳት ሥጋ በመመገብ ከእንስሳት ወደ ሰው በሚተላለፉ በሽታዎች እንደሚያጋልጥ ጥናቶችን በማጣቀስ ያመላከቱት የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ኅብረተሰቡ ይህን በመገንዘብ ከሕገ ወጥ ዕርድ ሊጠነቀቅ እንደሚገባ ተናግረዋል።

በተለይ በበዓላት ጊዜ ሕገ ወጥ ዕርዶች እንዳሉ የጠቆሙት የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ኅብረተሰቡ ጤናማነቱ የተረጋገጠ ሥጋ ከአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት፣ ከአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት ሥጋ ከሚረከቡ ሉካንዳ ቤቶች እንዲገበይ አመላክተው፤ የቁም እንስሳትን የሚገዙ የማኅበረሰብ ክፍሎች ወደ ድርጅቱ በመምጣት የእንስሳቱን የጤና ሁኔታ እንዲያስመረምሩ እና የዕርድ አገልግሎት እንዲያገኙ ጥሪ አስተላልፈዋል።

ሕገ ወጥ ዕርዶችን ለማስቆም መረጃዎችን የማሰባሰብ ሥራ እንደተሠራና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ወደ እርምጃ እንደሚገባም አስጠንቅቀዋል።

# ስፋሲካ በዓል

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከመጪው የፋሲካ በዓል ጋር በተያያዘም በቂ የምርት አቅርቦት ዝግጅት መድረጉን አስታውቀዋል።

ምንም እንኳን የሕዝቡ ቁጥር ከፍ ያለ ቢሆንም ኤጀንሲው ባቀደው መሠረት በቂ አቅርቦት ማዘጋጀቱን ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል። በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ገበያው ሚዛኑን እንዲጠበቅ የዋጋ ማነጻጸሪያ እንዲያገኙ፣ ለተጋነነ ወጪ እንዳይዳረጉና አማራጭ እንዲያገኙ ኤጀንሲው አቅሙና ካፒታሉ በፈቀደው በበቂ ሁኔታ መዘጋጀቱን አንስተዋል።

በፌዴራል ካለው ህብረት ሥራ ኮሚሽን አማካኝነት ምርት ካላቸው የክልል ማህበራት ጋር አብሮ ለመሥራት የመረጃ ትስስር መፍጠር ተችሏል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ለበዓል ፍጆታ የሚውሉ ምርቶችን በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ ወደ ሥራ እንደተገባም ጠቅሰዋል። በኤጀንሲው ሥር ካሉ 230 የሚሆኑ ሉካንዳ ቤቶች ያሉ ሠራተኞችና አመራሮች፣ መሠረታዊ ማህበራት፣ የመንግሥት መዋቅሩ ከጽዳት ጀምሮ እንዲዘጋጁና አቅርቦቱን እንዲያስተካክሉ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ የልኳንዳ ቤቶች በራሳቸው ግብይት ውስጥ ገበተው የሚገዟቸው የቁም እንስሳትን ሳይጨምር ኤጀንሲው ወደ 2ሺህ 800 የሚሆኑ የቁም እንስሳትን ወደ መዲናዋ እያስገባ ይገኛል። ከዚህ አኳያ በስጋ አቅርቦት በኑሮ ሁኔታ ዝቅተኛውንና መካከለኛውን የህብረተሰብ ክፍል ለማገልገል በቂ ዝግጅት ተደርጓል። በመሠረታዊ ሸቀጥ እንደ ፓልም ዘይትና ስኳር ያሉ፤ በግብርና ምርት እንደ ሽንኩርት ያሉት ምርቶች በብዛት ስለመኖራቸውም አስታውቀዋል።

የጤፍ ዋጋ በኪሎ ከ41 ብር ጀምሮ እየተሸጠ እንዳለና ህብረተሰቡ በስፋት የሚፈለገውን ምርት እየቀረበ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይ ጤፍ ላይ ከሌሎች የሸያጭ ገበያዎች በኩንታል ከአምስት መቶ እስከ ስድስት መቶ ብር ልዩነት እንዳለው አመላክተዋል። ጤፍ በሁሉም መሠረታዊ ማህበራት ከበቂ በላይ መኖሩንም ጠቁመዋል። እንደ ቅቤ፣ አይብ፣ እንቁላል፣ ዶሮና መሰል አቅርቦቶችንም በስፋት ለማሰራጨት እየተሰራ እንዳለ አስታውቀዋል። በኤጀንሲው በኩል ምርት ለተጠቃሚ የሚሸጡ ማህበራት በዋጋ ደረጃ የተሻሉ እንደሆኑና ካለው የገበያ ዋጋ አንጻር ዝቅ ተደርጎ ህብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲገለገል መደረጉንም ተናግረዋል።

የሚመጣው ምርት ከገበሬዎች ላይ በመሆኑ የጥራት ጉድለት እንደሌለውና ተዓሚኒ እንደሆነም ገልጸዋል። አንዳንድ ጊዜ የጥራት ችግር ሲያጋጥምም ምረቱ ወዲያው እንዲቀየር ይደረጋል ነው ያሉት።



# ‹‹ጠዋት ጠዋት አክቲቪስት፣

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ብቻ ሳይሆን ለተናገርነውም ኃላፊነትም አለብን ሲሉ አብራርተዋል።

በብልጽግና ሕገ ደንብ ውስጥ አንድ ሰው ወጥቶ በማሕበራዊ ሚዲያና በሕዝብ መገናኛ ብዙሃን በመናገር ሕገ ደንቡን ከጣሰም እንደሚጠየቅ ማወቅ እንዳለበት ነው ያሳሰቡት።

ጠዋት ጠዋት ብልጽግና ሆኖ ከሰዓት ከሰዓት አክቲቪስት መሆን እንደማይቻል አመልክተው፤ ይሄ ችግር ያለው እኛ ጋር ብቻ ሳይሆን ሁሉም ፓርቲ ጋር ነው። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል አክቲቪስት፣ የብልጽግና ፓርቲ አባል አክቲቪስት፣ የሆነ ድርጅት አባል ሆኖ አክቲቪስት መሆን ማለትም ለተሰለፈለት ዓላማ ያልተገዛ ማለት ነው። ይሄ ከፍተኛ ችግር ነው ብለዋል።

አክቲቪስትና ፖለቲከኛ መሆን ብቻ ሳይሆን፤ አክቲቪስትና ምሁርነትም ተቀላቅሏል ያሉት ዶክተር ዐቢይ፤ ምሁራን መረጃ የሚያገላብጡ፣ የሰበሰቡትን መረጃ የሚተነትኑና የመረጃቸውን ውጤት የሚያሳዩና የሚያመላክቱ መሆናቸውን ነው የተናገሩት።

አሁን ግን ጠዋት ጠዋት የዩኒቨርሲቲ መምህር ነው፣ ከሰዓት ከሰዓት አክቲቪስት ነው። አሰራሩ የተቀላቀለ ሆኗል። የተደራጀ መረጃ ይዞ ሳይሆን በክስተት ላይ የተመሰረተ መረጃ እያሰራጨ አዳዲስ አስተሳሰብ መገንባት የሚያስብ ኃይል ብዙ መሆኑን ተናግረዋል።

# ሰሞኑን በክልሉ የታየው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ቦታው ላይ በመገኘት አካባቢውን ያረጋጉ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ አካባቢው ላይ ሰላማዊ እንቅስቃሴ መኖሩን ገልጸዋል፡፡ የጸጥታ አካላቱም ማህበረሰቡን በማረጋጋት ቦታው ላይ ይገኛሉ፡፡ ከበፊቱ በተለየ ሁኔታም የሁለቱ ዞኖች አመራሮች እና የጸጥታ አካላት በቅንጅት እየሰሩ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

እንደ ቢሮ ኃላፊው ገለጻ፤ በግጭቱ ውስጥ ፖለቲካዊ ፍላጎት ያላቸው አካላትም ነበሩ፡፡ሰላም የማደፍረሱ ተግባር ከውስጥም ከውጭም ካሉ ጠላቶች ጋር በጋራ በመሆን የሚሰራ ነው፡፡በሁለቱ ዞኖች አካባቢ ሰላም ለማደፍረስ እና ሁለቱን ህዝቦች ለማጋጨት በተደጋጋሚ እንደሚሰራ ተናግረው በአካባቢዎቹ እና በሌሎች ቦታዎች ላይም የሚደረገው ሙከራ በጸጥታ ኃይሉ ጥበቃ እና ክትትል እንደሚመክን ገልጸዋል፡፡

ክልሉ ከትግራይ በሚዋሰንባቸው አካባቢዎችም በተለይም አሸባሪው ሕወሓት በወረራ የያዛቸው የተወሰኑ ቦታዎች ላይ ጥሩ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎች አሉ፡፡ አልፎ አልፎ በሁሉም ዞኖች አካባቢ በግለሰብ ግጭቶች የሚፈጠሩ ችግሮች ቢኖሩም ከአካባቢው አስተዳደር በላይ አይደሉም፡፡ ህገወጥ የመሳሪያ ዝውውር እና ህገ ወጥ ተኩስ አልፎ አልፎ የሚታይባቸው አካባቢዎችም መኖራቸውን የጠቆሙት አቶ ግዛቸው፤ ችግሮቹ በፍጥነት ካልተቀረፉ ሌላ ችግር ሊፈጥሩ እንደሚችሉ በመገምገማቸው ችግሩን ለመፍታት ሌት ተቀን እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

አቶ ግዛቸው እንደሚሉት፤ በጎንደር አካባቢም ጽንፈኛ የቅማንት ኮሚቴ የሚፈጥረው በየጊዜው የሚነሳ ችግር አለ፡፡ የሚፈጠሩት የጸጥታ ችግሮች ተመጋጋቢ መሆናቸውንም ጠቁመዋል፡፡ የውስጥም የውጭም ጠላቶች በጋራ ክልሉን የማተራመስ እና የማፍረስ ዓላማ እና ተልዕኮ ጭምር ይዘው እንደሚንቀሳቀሱ ተናግረዋል፡፡

ህገ ወጦችን መልክ የማስያዝ እና ወንጀለኞችን ወደ ሕግ የማቅረቡ ሥራ በሁሉም ዞኖች እና ወረዳዎች በስፋት እየተሠራ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡ የጽንፈኝነት እና አገር የማፍረስ አመለካከት እስካልደረቀ የተወሰኑ አካላትን አስሮ ለህግ በማቅረብ ብቻ የሚቆም ባለመሆኑ እዚህ ላይ በሚገባ መሥራት እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል፡፡ አለመግባባቶችን በዘላቂነት ለመፍታት አገራዊ ምክክሩ ወሳኝ መሆኑንም አክለው ገልጸዋል፡፡

አብዛኛው የክልሉ አካባቢ ትናንሽ ከሚፈጠሩ ችግሮች ባሻገር አጠቃላይ የልማት እና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን አቅዶ ለመስራት የሚያስችል ነባራዊ ሁኔታ በመኖሩ በአመዛኙ ሰላማዊ እንቅስቃሴ መኖሩንም ተናግረዋል፡፡

በክልሉ በውስን ቦታዎች ያሉ የጸጥታ ስጋቶችን ከፌዴራል መንግሥት እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የክልሉ መንግሥት ለማስተካከል ሰፊ ሥራ እየሰራ ነው፡፡ ሰላም በመንግሥት የጸጥታ መዋቅር ብቻ ሊረጋገጥ ስለማይችል መላው ህብረተሰቡ የህገ ወጦች መሸሸጊያ ባለመሆን እና ለህግ እንዲቀርቡ መረጃ በመስጠት እንደሁልጊዜው እንዲተባበር ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡

# ወደ ውጭ በሚላኩት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ተላልፏል።

ወደ አጎራባች አገሮች በሚላኩት የአትክልትና ፍራፍሬ ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ የተተመነው ከ50 ዓመታት በፊት እንደነበር አውስተው፤በዘርፉ የተሰማሩ ነጋዴዎችም ይህንን ክፍተት በመጠቀምም ከፍተኛ የሆነ ጥቅም እያጋበሱ እንደሆነ መስሪያ ቤቱ ባካሄደው ጥናት መረዳት መቻሉን ተናግረዋል።

እንደማሳያም የሀገር ውስጥና የጎረቤት አገራት ወቅታዊ የሙዝ ምርት መሸጫ ዋጋ ልዩነት ሲነጻጸር ከፍተኛ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ሙዝ በጎረቤት አገራት በኪሎ ከ8 እስከ 10 ብር እንደሚሸጥ በነጋዴዎች ሪፖርት የሚደረግ ሲሆን በኢትዮጵያ በመሀል አገር ገበያ የአንድ ኪሎ ዝቅተኛ የሙዝ መሸጫ ዋጋ 35 ብር መሆኑን አብራርተዋል።

ይህም የንግድ ሚዛኑን የሚያዛባና አገሪቱ የምታገኘውን ጥቅም የሚያሳጣ በመሆኑ በአገሪቱ ማዕከላዊ ገበያ ያለውን የሙዝ ዋጋ በመውሰድ፤ ክለሳና ማሻሻያ በማድረግ፤ በጎረቤት አገራት የአንድ ኪሎ ሙዝ ዝቅተኛ መሸጫ ዋጋ 37 ብር ተደርጓል ብለዋል።

በአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ላኪነት ተቀባይነት የተሰማሩት የአንድ ቤተሰብ አባላት መሆናቸው ለቁጥጥር አስቸጋሪ እንደነበር የተናገሩት ዳይሬክተሩ፤ የዋጋ ማስተካከያ መደረጉ በዚህ ረገድ የሚስተዋለውን ችግር ለመፍታት ያስችላል ብለዋል።

የዋጋ ማስተካከያው ቀደም ሲል የተደረጉ የንግድ ኮንትራት ስምምነቶችን ሊያፋልስ ይችላል በሚል ለ45 ቀናት እንዲራዘም መደረጉን የገለጹት አቶ መኮንን፤ የሽግግር ጊዜው እንዳበቃ የዋጋ ተመን ማሻሻያው ተግባራዊ እንደሚደረግ በብሄራዊ ባንክ በኩል ለሁሉም ባንኮች ሰርኩላር መተላለፉን አስረድተዋል።

አንዳንድ ሚዲያዎች የጂቡቲ መንግሥት ኢትዮጵያን በማስገደዱ የዋጋ ማሻሻያው እንደተነሳ አድርገው ያቀረቡት ዘገባ ከእውነት የራቀ መሆኑን አረጋግጠው፤ ጂቡቲም ሆነች ሌሎች ጎረቤት አገራት ለኢትዮጵያ በርካሽ የሚያቀርቡት ምንም አገልግሎት የለም፤ እኛም አንጻራዊ ጥቅም ልናገኝ በምንችልባቸው ጉዳዮች አበክረን መስራት አለብን ብለዋል።

አዲሱን የወለል የዋጋ ተመንን በተመለከተም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በድሬዳዋ ከሚገኙ ነጋዴዎች ጋር በመነጋገር መተማመን መፈጠሩንም አስረድተዋል። ነጋዴዎቹም በዘርፉ የሚስተዋለው የምርት ጥራት ችግር በምርቶች ዋጋ ላይ አሉታዊ አስተዋፅኦ ማድረጉንና መንግሥት በዚህ ረገድ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራ ያቀረቡት ምክረ ሃሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን አስረድተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ተሸፍኖ የማይቀረው በንጹሃን ላይ የተፈጸመው ግፍ ዛሬም ከፍ ብሎ ይሰማል!

ወጀብና ሌላም የሚረብሸው ኃይል የሌለበት በአንድ ቦታ የረጋ የውሃ አካል፤ ንጹህና የጠራ እንደመሆኑ በውስጡ ያሉ የተለያዩ ነገሮችን የማሳየት እድሉ ከፍ ያለ ነው፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ በውስጡ ያሉ ጎጂም ሆኑ ጠቃሚ የውሃ ውስጥ እንስሳቶችን በቀላሉ መለየት፤ ከሚጎዱት ለመጠበቅ፣ ከሚጠቅሙትም ለመወዳጀት እድል ይሰጣል፡፡ በአንጻሩ በወጀብና በማዕበል የሚናጥ የውሃ አካል ሁሌም የደፈረሰና በውስጡ ያሉ ጠቃሚም ሆኑ ጎጂ ነፍሳትን ለመመልከትም ሆነ ለመለየት የማያስችል እንደመሆኑ ጥሩ መደበቂያ ሆኖ ያገለግላቸዋል፡፡

ሕዝብም እንዲሁ ነው፡፡ ሰላም አግኝቶና የተረጋጋ ኑሮ ሲኖረው፤ በውስጡ ያሉ መልካምም ሆነ ክፉ ነገሮች የመጋለጥ እድላቸው የሰፋ ሲሆን፤ በአንጻሩ ሰላም ርቆት ዘወትር በጦርነትና ውጣ ውረድ ውስጥ እንዲያልፍ ሲደረግ በውስጡ ያሉ መልካም አድራጊዎችም ሆኑ እኩያን የመታየት እድላቸው ምንም ነው፡፡ አሸባሪው ሕወሓት በደረሰበትና ባለበት ሁሉ የሚሆነውም እንዲሁ ነው፡፡ ምክንያቱም ቡድኑ በጫካ ሳለም ሆነ በመንግስትነት መንበሩ ላይ በተቆናጠጠባቸው ጊዜያት፤ ሃገር እንደ ሃገር፣ ሕዝብም እንደ ሕዝብ የተረጋጉ ሆነው እንዳይኖሩ በርካታ ስራዎችን ሰርቷል፡፡

ይሄን የሚያደርገው ያለምክንያት አልነበረም፡፡ ዝም ሲል ስለሚጨንቀው፤ የተደላደለ ሕዝብ የጎደለበትን ለይቶ ስለሚጠይቀው፤ ከፍ ሲልም የቡድኑ እኩይ ተግባራት ስለሚጋለጡ፤ ሕልውናውን በሰላም ውስጥ ሳይሆን በነውጥና ቀውስ ውስጥ በመመስረቱ ነው፡፡ ይህ ግን አስተውሎት የጎደለው ስልት ነበር፡፡ ምክንያቱም ሕዝብ ምንም እንኳን በሁከትና መለያየት ውስጥ እንዲኖር ቢፈረድበትም፤ ግፍ ሲበዛ ግፉዓን ሳይነጋገሩ የሚግባቡበት የጋራ ህልውና ማስጠበቂያ እሴት ያላቸው ስለሆነ ነው፡፡ ለዚህም ነው በ2010 ላይ ሳይነጋገር የተግባባው ሕዝብ በሕዝባዊ ማዕበል ቡድኑን ከስልጣን ያስወገደው፡፡

ይሁን እንጂ ቡድኑ ያለ ጥፋትና ጦርነት መኖር ስለማይችል፤ የትግራይን ሕዝብ ከወንድሞቹ ነጥሎ የሕልውናው ማቆያ ሊያደርገው ወሰነ፡፡ እናም በጦርነት ነጋሪት ጉሰማ የጀመረውን ራስ የማቆየት ትግል ወደ ዋና ዋሻው ጦርነት ጎትቶ አስገባው፡፡ የጦርነት ጉዞውን ለማዝለቅና በጦርነት ውስጥ ተደብቆ ለመኖር ካለው ሕልም የተነሳም ወደ አማራ እና አፋር ክልሎች ለወረራ ተሰማራ፡፡ ለራሱ ሕልውና ሲል በነደፈው ጦርነትም በርካታ ንጹሃንን በግፍ ገደለ፤ በርካቶችን ለአካል ጉዳት ዳረገ፣ በርካቶችን አስገድዶ በቡድን ደፈረ፣ በርካታ ሃብትና ንብረት አወደመ፡፡ በዚህም በአፋርና አማራ ክልሎች የከፋ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሥነልቡናዊ ቀውሶችን ፈጠረ፡፡

ከሽብር ቡድኑ መናወጥ ካረፉበትና መረጋጋት በተፈጠረባቸው አከባቢዎች እየተጋለጠ የመጣው ይህ አይነት ግፍና በደል ደግሞ ቡድኑ ለ40 ዓመታት እንደ አገር ከፈፀማቸው ግፍና በደሎች የቀጠለ ሲሆን፤ ይሄን እውነትም በርካቶች ሲያጋልጡና የግፉዓንን እንባ ለማበስ ሲታትሩ ቆይተዋል፡፡ ከሰሞኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ባወጣው ሪፖርት መሰረትም በአማራ ክልል ከ1 ነጥብ 8 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ቋሚ ድጋፍ የሚሹ ሲሆን፤ ከ1ሺህ217 በላይ ዜጎች ጾታዊ ጥቃት ደርሶባቸዋል፡፡ በአፋር ክልልም የቁጥር ልዩነት ቢኖርም ተመሳሳይ ድጋፍ የሚሹ እና የመደፈር ጥቃቶች የተፈጸመባቸው ያሉ ሲሆን፤ በክልሉ በጦርነት ምክንያት በትምህርት፣ በጤና ተቋማትና በመንግሥት ተቋማት፣ በግለሰብ ቤቶችና በዕምነት ተቋማት ላይ የደረሰው ውድመት በብር ሲሰላ ከ800 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ነው፡፡

ተቋሙ በአማራና አፋር ክልሎች የዳሰሳ ቁጥጥር ጥናት አከናውኖ ካወጣው ሪፖርት ለአብነት በአማራ ክልል የሆነውን ለማሳየት ያህል፤ በክልሉ የጦርነት ቀጠና በነበሩ ሰባት ዞኖች በተለያዩ ምክንያቶች ከቀያቸው የተፈናቀሉና ቋሚ ድጋፍ የሚሹ ዜጎች በከአንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን በላይ ናቸው፡፡ ከተፈናቀሉት ባሻገርም ሴቶችና ህጻናት ለጾታዊ ጥቃት ሰለባ ሆነዋል። በዚህም በሰሜን ጎንደር 56፣ በደቡብ ጎንደር 89፣ በሰሜን ወሎ 548፣ በዋግህምራ 111፣ በደቡብ ወሎ 342፣ በሰሜን ሸዋ 119፣ በኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ስምንት በድምሩ 1ሺህ217 በላይ እናቶች፣ ልጃገረዶችና አረጋውያን ተደፍረዋል፡፡

በንብረት በኩልም በክልሉ በሚገኙ የመንግሥት፣ የግልና የሕዝብ ተቋማትና ንብረቶች እንዲሁም ሃይማኖት ተቋማት ላይ የከፋ ጥፋት ደርሷል፡፡ በዚህም የትምህርት፣ የጤናና ሌሎች አገልግሎት መስጫ ተቋማት በጦርነቱ ወቅት እንደ ካምፕ፣ የሕክምና መስጫና ልዩ ልዩ መገልገያ ሆነው አገልግለዋል፤ እንዲሁም ሆን ተብሎ ተዘርፈዋል፤ ተቃጥለዋልም፡፡

የሽብር ቡድኑ በዚህ መልኩ በአማራም ሆነ በአፋር ክልሎች ያደረሳቸውን ጉዳቶች ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽንም ሆነ በመገናኛ ብዙሃን በተደጋጋሚ የተገለጹ፤ ግፎቹም የተነገሩ ቢሆንም፤ ይሄን እውነት መቀበል የማይፈልጉት የሽብር ቡድኑ ጋላቢዎች ግን ዛሬም ከእውነትቱ በተቃራኒ ለሚነሱ የጅራፍ ድምጾችን በማስተጋባት ላይ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም ቢያፍኑት የማይታፈነው፤ ቢደብቁት የማይደበቀው፤ ቢቀብሩት ጭምር ተቀብሮ የማይቀረው የግፉዓን ግፍ ጊዜ እየጠበቀ ዛሬም ድረስ ከፍ ብሎ እየተደመጠ ይገኛል!


እፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡**

## የምትሄድበት እንዳይጠፋህ የመጣህበትን አትርሳ

**ከአስባቸው ደሳለኝ አበሻ (ለንደን)**

እንደምን ሰነበታችሁልኝ ውድ የአዲስ ዘመን አንባቢዎች፤ የዛሬ አራት አመት ገደማ ዶክተር ዐቢይ፣ የለውጥ ችቦ ለኩሰው በድል አድራጊነት በጨለማው 27 አመት ጥፍር ነቃይ ስርአት ማክተሙን ሲያበስሩልን፤ የክርስቶስን መስቀል ተሸክመው እንደመጡ ያህል ቆጥረን በእልልታና በሆታ ሐገር ምድሩ እስኪጠበን ድረስ ከአፍሪካ እስከ ሰሜን አሜሪካ፣ ከአውሮፖ እስከ ሚዲልኢስትና እሩቅ ምስራቅ፣ ሳይቀር እልል ብለናል። እርሳቸው ይዘው የተነሱት የመደመር አስተሳሰብም የሚችና የጎዳይ አንድነት ሳይሆን፤ መደመር ፍልስፍና ነው በማለት አስደምመውናል። ፍልስፍና ደግሞ ጥበብ በመሆኑ አሮጌን ስርአት ቀብሮ አዲስ ስርአት ለማዋለድ የምንከተለው የፍልስፍና ርዮታአለም መሆኑን በተደጋጋሚ ሲገለጥ እንደሰማነው የፍልስፍና ዋና አላማውም ስርአትን ማስፈን መሆኑን አስረግጠው ሲያበስሩልን የኢትዮጵያ ትንሳኤን ለማየት የጓጓው ሁሉ የንቢቱን ቲሸርት እየቀየረ የዶክተር ዐቢይን ፎቶግራፍ ደረቱ ላይ ያልለጠፈ አልነበረም፡፡

ዋናው የመደመር አላማ ሰዎችን በሰላማዊና፣ ፍትሀዊ በሆነ ህብረተሰብ ውስጥ በጋራ ተባብረው ተደጋግፈው እንዲኖሩ የሚያስችል የአዲስ ስርአት አዋላጅ መሆኑን በሐሳብ ደረጃ ተስማምተናል። ምክንያቱም የሰው ልጆች እንደመሆናችን መጠን ሁልግዜም አዳዲስ ነገርን ማየት ብቻ ሳይሆን አዲስ ስርአትም በአስተማማኝ ሁኔታ አገራችን ላይ ተመስርቶ ለማየት በመፈለጋችን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በደስታ ሰክሮ ከጫፍ እስከ ጫፍ ሆ ሲል፤ ከአኩራፊው የሕወሓት ቡድንና ሸኔ በቀር ያልደገፈ አልነበረም። ይህንን መካድም አይቻልም፡፡ ጭራሽ የምስራቁ አለም ፍልስፍና መነሻ የሆነችው ኢትዮጵያ የሐበሻ ተወላጆች የኮከባቸውን ሀያልነት በመጠቀም ወደ አረቡ አለም በመገስገስ የምድራችንን የፍልስፍና መንገድ ቀይሠዋል፣ እየተባለ በታሪክ ተመራማሪዎች ሲነገር ብዙዎቻችን ቀልድ ይመስሉን የነበሩት እውነተኛ ታሪኮች በእኛ ትውልድ በጠቅላይ ሚ/ር አብይ የመደመር ፍልስፍና ልናረጋግጥ እንችላለን በሚል ተስፋ ሁላችንም ቆመን የዛሬ አራት አመት አጨብጭበናል፡፡

ይሁን እንጂ ይሁዳ በ30 ዲናር ፈጣሪውን አሳልፎ እንደሰጠ ሁሉ፤ ደስታችንን አጣጥመን ሳንጨረስ ለጥቅማቸው ሲሉ ሰው ሳይሆን አገር አሳልፈው የሚሰጡ ኃይሎች (የትግራይ ወያኔዎችና ሸኔ) በከፈቱብን የህልውና ጦርነት ምክንያት በኢትዮጵያ የለውጥ ታሪክ ውስጥ ብዙ ውጣ ውረዶችን አይተን ዋጋ ከፍለንበታል። በመከራና በጦርነት፣ በስደትና በመፈናቀል፣ በርሀብና በበሽታ ከብርሐን ተስፋ በተቃራኒም ህይወትና ሞትን መውደቅና መነሳት የፈተናና የድል ተምሳሌትነትን ያየንበት የኛ ትውልድ መስታወት በመሆኑ አሁንም ቢሆን ለውጡን ከነ ድክመቱ የምንደግፍበት በቂ ምክንያት አለን፡፡ በሐገር ውስጥና በመላው አለም የምንገኝ ኢትዮጵያውያኖች በወያኔ አረመንያዊ አገዛዝ ስንገፋ ኖረናል፡፡

በአንጻሩ ያሳለፍነውን የ27 አመት የመከራ ዘመን ብዙዎቻችን ፈፅሞ አንረሳውም፡፡ እኛ ብቻ ሳንሆን ወገኖቻችን ይደርስባቸው የነበረውን ሰቆቃ ቆዳቸው እስኪ ገፈፍ ድረስ የተገረፉትን ስቃይና እስራት ሳንጨምር፤ ስርአቱን ለመሸሽ ሲሉ ከአገር ለመሰደድ በሊቢያ በርሀ ሲያቋርጡ አንገታቸውን የተቀሉት ወንድሞቻችችን ዛሬም ነገም ፈፅሞ አንረሳቸውም፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ ከወያኔ ባልተናነሰ ሁኔታ ለመከራችን መብዛት በጥቅማጥቅም የተገዙት ሆድ አምላኪ ባንዳ የቀድሞ ባለስልጣኖች ተልኳቸው ለመወጣት እንደ ይሁዳ ሐገር ከድተው አሳልፈው ለባእዳን እየሰጡን፣ በአሜሪካን ኮንግረስና በአውሮፖ ፓርላማዎች ሲያስከስሱን የነበሩ የወያኔ ቅጥረኞችና የሸኔ አሸባሪዎችን ታግለን አፈር ከድሜ አስገብተን በደም ቀለም የተፃፈ ታሪክ ጀርባቸውና ግንባራቸው ላይ አትመን በድል አድራጊነት ኢትዮጵያን ወደ ከፍታ ይዘን እየገሰገስን ነው፡፡

ሆኖም ግን የሕወሓት አሸባሪ ቡድን ዶሮ ሳይጮህ ያደረጉት ክህደት አገሪቱን ወደ እልቂትና ወደ ትርምስ ለማምራት በሰሜኑ ጦር ላይ የወሰዱት የክህደት ጭፍጨፋ ተከትሎ በተፈጠረው ሁከት አሁንም ድረስ የሐገሪቱ ሰላም በቅጡ አልተረጋጋም። እንዲያውም ያሳለፍነው የአንድ አመት ተኩል ጦርነት አልበቃ ብሎ ለሁለተኛ ዙር ጦርነት እየተዘጋጁ ጦር እየሰበቁ የጦር መሳሪያ እየወለወሉብን መሆኑን እንሰማለን፡፡ መንግስት ለሰላም የሚያደርገው የተለሳለሱ እርምጃንም እንደ ፍርሀትና እንደ ተሸናፊነት ቆጥረው ለትግራይ ሕዝብ እርዳታ እንዳይደርሰው ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም፡፡

አሁንም በመቀራረብ መወያየትና መፍትሔ መሻት ሲቻል ፀብ ያለሽ በዳቦ የሚለው በደብረ ጽዮን አማካኝነት የሕወሓት ዲስኩር ላይ እንደተናገሩት ከመንግሥት ጋር በተለያዩ ወገኖች አማካይነት ንግግር እየተደረገ መሆኑን አመልክተዋል። ሆኖም ግን ንግግሩ ለድርድር የማይቀርቡ ጉዳዮች እንዳሉበት ጠቁመው በንባብ አሰምተውን አዳምጠናል። በዚህም መሠረታዊ የትግራይ ሕዝብ ጥያቄዎች ናቸው ያሏቸውን አምስት ጉዳዮችን ዘርዝረዋል። “በመጀመሪያ ደረጃ በሠራዊታችን ላይ አንደራደርም አሉ። አሁን ያለው ብቻ ሳይሆን ገና እንጨምርበታለን። ስለዚህ በሠራዊታችን ጉዳይ ላይ ድርድር ብሎ ነገር አይታሰብ ብለውናል። ከዚህ በኋላም ኃይላችንን ይዘን ነው የምንኖረው” በማለትም አቋማቸውን ነግረውናል።

በተጨማሪም በአገሪቱ ሕገ መንግሥት የታወቁ የትግራይ ክልል ወሰን ጉዳይ፣ የኤርትራ ሠራዊት ከትግራይ መውጣት፣ የትግራይ ሕዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን መብት ጉዳይ እና በትግራይ ሕዝብ ላይ በደል የፈፀሙ ግለሰቦች ተጠያቂነት ለድርድር አይቀርብም በማለት አቋማቸውን ግልፅ፣ አድርገዋል። በድርድሩም ጥረቶች ውስጥ እነዚህ አምስት ቅድመ ሁኔታዎች ዋነኞቹና ሊጣሱ የማይገቡ የድርድር ነጥቦች መሆናቸውን ጠቅሰው “ሰጥቶ መቀበል” የሚባለው ጉዳይ እዚህ ላይ አይሰራም” በማለት ለወደፊቱን ለሚደረገው ሐገራዊ ውይይትም ሆነ የሰላም ድርድር. ለማጨናገፍ. በአተካሮ የተሞላ ሀሳብ ሰንዝረዋል። በኔ እምነት ይህ የጤንነት ምልክት አይመስለኝም። የምትሔድበት እንዳይጠፋህ የመጣህበትን አትርሳ ይባላል፡፡

በእርግጥ ምኞት አይከለከልም የደብረ ፅዮንም ሆነ ደጋፊዎቻቸው፣ ሊያውቁት የሚገባ ጉዳይ ግን ተወደደም ተጠላም ኢትዮጵያ ትነሳለች። እንደ ንጋት ፀሀይ በርታ እንደ ውድቅት ጨረቃ ደምቃ እድሜ ከሰጣቸው ኢትዮጵያ ተነስታ ይመለከታሉ!። ኢትዮጵያ በላይዋ ላይ ያለውን የወያኔና የሸኔ ቆሻሻ ጥቀርሻን አፅድታ ትነሳለች፡፡ ኢትዮጵያ ካጋጠማት ክፉ የዘረኝነት ደዌ ተላቃ እንደገና እንደ ብርቅዬ አልማዝ ሆና ታበራለች። ኢትዮጵያ ከወረራት የመከራ ከበባ ተላቃ፤ ልጆችዋን ካስመረራቸው ክፉ አሳቢና እኩይ መርገምት ነፃ ወጥታ ከተሰደዱበት የአለም ዳርቻ ልጆቿን ሰብስባ በአምላኳ ሀይል የአፍሪካ ራዕይ የአለም ተስፋ ሆና እንደገና ትነሳለች፡፡ ወደፊት አለም በስምምነት የሚያከብራት ውብ ሐገር አስገራሚ ታዕምራት የሚታዩባት ለአለም ሁሉ የተሰጠች የተቀደሰች ሐገር ሆና ከፍ ትላለች።

በታሪክ ውስጥ የመጀመሪያ ኮሎናሊዝምን ያንበረከከች የጥቁር አልማዞች ሐገር ኢትዮጵያ፣ የአሪኪዎለጂ ምስጢሮች ሲወጡ የአፍሪካ መዲና ዋና ከተማ አዲስ አበባ በብሔራዊ ጀግኖች አደባባዮቿ ያሸበርቁበታል፡፡ ሁሉም ለጀብድ የተዘጋጁ በሚመስሉ በጥንታዊ ብሔራዊ ጀግኖች የተጋድሎ ታሪክ በሚዘክሩ ሐውልቶች ኢትዮጵያ ደምቃ እያበራች ትከበራለች፡፡ እነዚህ በቅኝ ግዛት ያልተገዙና በታሪክ ባለሐብት ጥቁር አልማዞች አለምን የሚያስደምሙበት ቀን እሩቅ አይሆንም፡፡ አለም የሰው ልጅ ጨራሹን የኒኩለር ቴክኒዎሎጂ እየሰማ መጨነቁን አቁሞ በዚች በተቀደሰች ሐገር ቱሪስት ሆኖ እየጎረፈ ሲጎበኛት ጣፋጭ ምግቦቿን በእጃቸው ቆርሰው እየተደነቁ መመገብን ሲመርጥ አብረን የምናይበት ቀን እሩቅ አይደለም። ስለዚህ እውነትን እንጂ ጊዜን ተደግፈህ አትቁም ጊዜ ባለበት አይቆምም ይሔዳል ይመጣል፡፡ ከጊዜ ጋር ለመራመድ ደግሞ የምትሔድበት እንዳይጠፋህ የመጣህበትን አትርሳ፤ እኔም ለዛሬው በዚሁ አበቃሁ፡፡ በሌላ ጽሑፍ እስክንገናኝ ቸር ይግጠመን።

Website - www.press.et Email - addiszemen@press.et Facebook - Ethiopian Press Agency

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

# ነፃ ሃሳብ



**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## (ፖለቲካዊ ትክክለኝነት አሁኑኑ ... ! ?

በበርካታ ፈተናዎች፣ ቀውሶችና ጫናዎች ታንቆ እንዳለ ሕዝብ ፤ በአስቸጋሪ ለውጥ ሒደት ላይ እንዳለች አገር ፤ የቀደሙ ሶስት አገዛዞች እዳ ተሸካሚ እንደሆነ አገር፣ ሕዝብና አመራር ፤ ሕወሓትንና ሸኔን የመሰለ ጠላት እንዳለው አገርና ሕዝብ ፤ ጽንፍ የረገጠ አቋም በሚራገብበት ፖለቲካዊ ምህዳር እንዳለ መልክዓ፤ ለግማሽ ክፍለ ዘመን ጎሰኝነት፣ ጥላቻና ልዩነት ተቋማዊና መዋቅራዊ ሆኖ ሲቀነቀንበት እንደ ኖረ አገር ፤ ድርቅ፣ ጦርነትና መፈናቀል እንደ ጎን ውጋት ቀስፎ በያዛት አገር፤ የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት አረፋ እያስደፈቀው ያለ ኢኮኖሚ ባለበት ፤ በጎሳና በቋንቋ ላይ የተመሰረተ ፌደራላዊ ስርዓት እንዳቆመ አገር ፤ በማንነት ፍላጎቶች እና ጥያቄዎች እንደሚሳሳብ ሕዝብ ፤ የሕግ የበላይነት ክፍተት እንደሚስተዋልበት አገር፤ ያደሩና ያልተመለሱ ጥያቄዎች እንዳሉት ሕዝብ ፤ የተሳሳተ ትርክት ሰለባ ያደረገውና ሆድ የባሰው ሕዝብ እንዳለበት አገር ፤ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ከካርታ ሊፍቁን በጥፍራቸው አሰፍስፈው በቆሙበት በዚህ ቀውጢ ሰዓት፤ ከዚህ ሁሉ ድቅድቅ ዋሻ ባሻገር የተስፋ ጭላንጭል በምናይበት አገር፤ ወዘተረፈ. ፖለቲካዊ ትክክለኝነት Political Correctness (PC) የልብ ትርታው መሆኑ ለቅፅበት እንኳ ሊዘነጋ አይገባም።

ለውጡ ከባለፉት 48 ወራት ወዲህ እንኳ ብዙ ብዙ ዋጋ እያስከፈለን ይገኛል። በገለልተኛ ወገን በጥናት ባይረጋገጥም በለውጡ ተቀባይነት legitimacy ላይ ያስከተለውን አሉታዊ ተፅዕኖ በአብነት ማንሳት ይቻላል። የሴራ ፖለቲካና የበሬ ወለደ "ወሬ" ከፖለቲካ ትክክለኝነት ልምሻ ጋር ተጃምሎ፣ አብሮ እንደ ሰደድ እሳት ሲዛመት ታዝበናል። በሁለቱ እኩይ ኃይላት መካከል ማለትም በሴራና በፖለቲካዊ ኢትክክለኝነት ያለውን እሳትና ጭድነት ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ተከስተው ከነበሩ ግጭቶች አኳያ ያስተውሏል። ሰሞነኛው የአማራ ብልጽግናና የኦሮሞ ብልጽግና አንዳንድ ከፍተኛ አመራሮች ቁርቁስ እንዲሁም የአብንና የኦፌኮ እሰጥ አገባ አገሪቱ የምትገኝበትን ተጨባጭ ሁኔታ በቅጡ ካለመረዳትና ከሕዝበኝነት (populism) የመነጨ አደገኛ አሰላለፍ ነው።

ይህ ሕዝብ አስተዋይና አርቆ ተመልካች ባይሆን ሊያስከትለው የሚችለውን አደገኛ ዳፋ ልብ ማለት ያሻል። የሚያሳዝነው ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ይህን አደገኛ መንገድ መከተላቸው ነው። ዛሬ ባልና ሚስት እንኳ በልጆቻቸው ፊት ከረር ያሉ ቃላትን ላለመለዋወጥ በሚጠነቀቁበት 21ኛው መ.ክ.ዘ ይህን ታላቅ ሕዝብና ጥንታዊት አገር የሚመሩ የገዢው ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች እንካስላንትያ አሽኮለል ሲገጥሙ መስማት፤ በእርግጥ ይሄ ሕዝብ የሚገባውን መሪ አግኝቷል የሚል ጥያቄ እንዳነሳ አስገድዶኛል። ምንም እንኳ ጨዋና ስለሚናገሩት ነገር የሚጨነቁና የሚጠበቡ መሪዎች መኖራቸው ባይካድም። በምሳሌ ለመምራት ሌት ተቀን የሚማስኑ መሪዎች ቢኖሩም።

የፖለቲካዊ ትክክለኝነትን አንድምታዊና ታሪካዊ ዳራ በስሱ ከሸመን በኋላ ወደ አገራችን ፖለቲካዊ መልክዓ አውርደን እንከናነበዋለን። ከንብንቡን ግን ለአገራችን ለሕዝባችን ክብር ስንል መልሰን እናወርደዋለን። ፖለቲካዊ ትክክለኝነት በ1930ዎቹ ጀምሮ ጥቅም ላይ እንደዋለ የተለያዩ በዘርፉ ላይ የተከተቡ ድርሳናት ያትታሉ። ወደ ኋላ ተመልሰን ይሄን ዘመን ስንቃኝ የዘር፣ የሃይማኖት፣ የፆታ፣ ሰብዓዊ መብት፣ የእኩልነት ጥያቄዎች ወዘተረፈ. ጮህ ብለው መሰማት የጀመረበት ነበር። ፅንሰ ሀሳቡ በዚህ ተመሳሳይ ዘመን ጥቅም ላይ መዋል የጀመረበት መግፍኤም ይሄው ነው። በሌላ በኩል ፅንሰ ሀሳቡ ከግራ ዘመም አይዶሎጂ ማለትም ከሶሻሊስትና ኮሚኒስት ርዕዮት ጋር ተያይዞ እንደመጣ ይነገራል። ሆኖም ብያኔው ግን በርዕዮት ዓለሙ ልክ የተሰፋ ነው።

የፓርቲውን ሕገ ደንብ የሚያከብር መሪ ወይም አባል እንደ ፖለቲካዊ ትክክለኛ ይቆጠራል። በ1980ዎቹ አጋማሽ ደግሞ ሀሳቡ ከተለያዩ የስርዓት ትምህርት ማሻሻያ ፕሮግራሞች እና ከአካዳሚያዊ ነፃነት ጋር ተያይዞ ይወሳ ነበር። ይሁንና እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1991 ፕሬዝዳንት ጆርጅ ቡሽ በሚቺጋን ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች የምረቃ ስነ ስርዓት ላይ ስለ " ፖለቲካዊ ትክክለኝነት" አሳሳቢነት ከተናገሩ ወዲህ ፅንሰ ሀሳቡ ከስርዓተ ትምህርት ክለሳ፣ ከምረቃ ስነ ስርዓት ንግግር ደንብ፣ ከጾታና ዘር ጥቃት፣ ወዘተረፈ ጋር መያያዝ ጀመረ። የፅንሰ ሀሳቡ ተገዳዳሪዎች ደግሞ ከአስተሳሰብ ፖሊስነት thought police እና መልካም ስምን ዝናን ከማጥፋት፣ ከማጉደፍ (McCarthyism) ጋር ያያይዙታል። ሆኖም ፖለቲካዊ ትክክለኝነት ፖለቲካን ከሁሉም ማለትም ከሰብዓዊነት፣ ከፍትሐዊነት፣ ከእኩልነት፣ ከግልፅነት፣ ከተጠያቂነት፣ ከመብት፣ ከአብሮነት፣ ከእርቅ፣ ከሰላም፣ ከመነጋገር፣ ከመቀባበል፣ ከመደማመጥ ወዘተረፈ. አስበልጦ የመመልከት መጥፎ አባዜን መሞገት ነው።

ፅንሰ ሀሳቡ ስራ ላይ ከዋለ ከ80 አመታት በኋላም ፖለቲካዊ ትክክለኝነት ዛሬም አወዛጋቢ፣ አነጋጋሪ ነው። በተለይ የአሜሪካው የቀድሞው ፕሬዝዳንት ዶናልድ ትራምፕ በቲዊተርም ሆነ በመደበኛ ሚዲያዎች መግለጫ ከመስጠታቸው በፊት ማንን እንደሚያስቀይም ? የማንን መብት እንደሚጋፋ ? የንግግራቸው፣ የቲውታቸው ትርጉሙ፣ አንድምታው ምን ሊሆን እንደሚችል አስቀድመው ስለማያመዛዝኑ ከፖለቲካዊ ትክክለኝነት አንጻር በተደጋጋሚ ነጥብ ሲጥሉ ይስተዋላል። ቲዊት ባደረጉ ለጋዜጠኞች መልስ በሰጡ ቁጥር ፊደላቸው፣ አፋቸው ወለም እያለው ምህረት የማያውቀው ሚዲያም እግር በእግር እየተከተለ ሲያብጠለጥላቸው እሳቸውም አፋቸውን ጣታቸውን መሰብሰብ ቢቸግራቸው እውነቱን መዘርገፍ እንጂ ፖለቲካዊ ትክክለኝነት ጉዳዬ አይደለም ማለት ጀመሩ። በእርግጥ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ማለትም ሚዲያ፣ ሕግ አውጭና ተርጓሚ፣ ሲቪል ማህበራት፣ ወዘተረፈ . ባለበት አገር የፕሬዝዳንቱም ሆነ የፖለቲከኞች፣ የጋዜጠኞች፣ የተሚጋቾች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ ወዘተ. የአፍ ወለምታ ሆነ ፖለቲካዊ ኢትክክለኝነት ሳይውል ሳያድር በቅቤ ስለሚታሽ ስለሚታረም ያስገምትና ያስተዛዝብ ይሆናል እንጂ ያን ያህል ዘላቂ ጉዳት አያደርስም።

ፕሬዝዳንት ትራምፕ ስልጣን ላይ እያሉ አስተዳደራቸው ከሳኡዲ አረቢያ ጎን የሚቆመው "ለምናደርግላት ወታደራዊ እገዛ እጅ በእጅ በጥሬው ስለምትከፍለን ነው።" በማለት የሳቱት ፖለቲካዊ ትክክለኝነት የአሜሪካ ወታደሮች ለግዳጅ የሚሰማሩት የአገራቸውን ደህንነት፣ ብሔራዊ ጥቅምና እሴት ለማስከበር እንጂ በቅጥረኛ ነፍሰ ገዳይነት mercenaries አይደለም በሚል ከግራም ከቀኝም አቧራ አስነስቶ ነበር። ፕሬዚዳንቱ ትውልደ ሶማሊያዊ ሴት የምክር ቤት አባልንና ሌሎችን ሶስት ባልንጀሮቿን" የምንሰራው ነገር ካልተዋጠላቸው ወደ አገራቸው መመለስ ይችላሉ።..." ከዚያ በፊት ደግሞ ሴቶችን፣ ቀደምት አሜሪካውያንን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ አፍሪካውያንና ሜክሲኮአውያን በተመለከተ አይደለም ከአሜሪካ ፕሬዝዳንት ትላንት ከተወለደ ብላቴና የማይጠበቅ ነውረኛ ነገር በመናገራቸው ማወዛገቡ ይታወሳል። በአሜሪካ ታሪክ እንደ ትራምፕ ደጋግሞ ነጥብ የጣለ የለም የተባለው ለዚህ ነው። የአንድ ጊዜ ፕሬዝዳንት ሆነው የቀሩትም ለዚህ ነው።

በሽግግር ወይም ገና በመሰራት ላይ ላለች እንዲሁም አንድነቷ በቋፍ ላይ ለሚገኝ አገር ግን ፖለቲካዊ ትክክለኝነት የልብ ትረታዋ ነው። እንደ 'ጥላ ወጊ'(stroke) በድንገት ሊጥላት፣ ሽባ አድርጎ አሳስሮ የአልጋ ቁራኛ ሊያደርጋት ይችላል። ለውጡን ሊቀለብሰው ከፍ ሲልም ወደለየለት ብጥብጥ ሊዘፍቀን ይችላል። ለመሆኑ ፖለቲካዊ ትክክለኝነት ምንድን ነው?

መሪዎች፣ ፖለቲከኞች፣ ተሚጋቾች፣ ጋዜጠኞች፣ ልሒቃን፣ መምህራን፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ አባ እማ ወራዎች፣ በአጠቃላይ ሰዎች አንድን ቡድንም ሆነ የሕብረተሰብ ክፍል የሚያስከፋ፣ የሚያስቆጣ ንግግርም ሆነ ሌላ ያልተገባ ድርጊት መፈፀም እንደሌለባቸው የሚያሳስብ ፅንሰ ሀሳብ ፖለቲካዊ ትክክለኝነት ይባላል።

አገራችንም በፖለቲካዊ ኢትክክለኝነት የምትንጠራወዝ፣ የምትላጋ፣ የምታተኩር(Obssesed) ናት ማለት ይቻላል። በተለይ ከለውጡ ወዲህ በአዳራሽ፣ በአደባባይ፣ በመደበኛ ሚዲያ፣ በማህበራዊ ሚዲያ፣ ወዘተ. በለውጥ ኃይሉ፣ በተፎካካሪው፣ በተሚጋቹ፣ በልሒቁ፣ በአገር ሽማግሌው፣ በሃይማኖት መሪው፣ በታዋቂ ሰው፣ ወዘተረፈ . በተደረጉ ንግግሮች፣ በተሰጡ አስተያየቶች፣ መልሶች፣ በተላለፉ ንግግሮች፣ በመግለጫዎች፣ ወዘተ. የፖለቲካዊ ትክክለኝነት ልምሻዎች ተከስተው ያስከፉት ብሔር፣ ሃይማኖት፣ ማንነት፣ አይዶሎጂ፣ " መስመር "፣ ወዘተረፈ . ወገን አለ ። ይሁንና የፖለቲካዊ ትክክለኝነት ሆን ተብሎም በአፍ ወለምታም ሊጣስ ይችላል። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ወደ ኃላፊነት እንደመጡ ወደ ተለያዩ ክልሎች በመዘዋወር ሕዝብ ባነጋገሩ ወቅትም ሆነ ከዚያ ወዲህ የተለያዩ ፖለቲካዊ ትክክለኝነትን የሚያስነሱ ግርታዎችን ቀስቅሰው ነበር። ሆኖም በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ የፖለቲካዊ ትክክለኝነት ጥያቄ ያስነሱባቸውን ሀሳቦች ያብራራሉ ። ያስረዳሉ ።

የቀድሞው የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ "አክሱም ' ለወላይታ ' ምኑ ነው ? " እንዲሁም የተወለዱበትን ሕዝብ ስም ጠርተው "... ከዚህ ወርቅ ሕዝብ መፈጠሬ ያኮራኛል ። ..." በማለታቸው ከፖለቲካዊ ትክክለኝነት አንጻር ትልቅ ነጥብ አስጥሏቸው ነበር ። ፓርቲን ከሕዝብ ጋር ማመሳሰል፣ ገዥ መደብን ከአንድ ብሔር ጋር ማያያዝ፣ አንድን ዕምነት ከአንድ ብሔር ጋር ማቆራኘት፣ ሰንደቅ አላማን ከአንድ ቤተ ክርስቲያንና ጎሳ ጋር ማመሳሰል አንድ ማድረግ እንደ ዜጋም እንደ አገርም ሁልጊዜ የምንስታቸው የፖለቲካዊ ትክክለኝነት ኢላማዎች ናቸው።

በተለይ በአዲስ አበባ የኢሬቻ በዓል በታላቅ ድምቀትና በሰላም ለመጀመሪያ ጊዜ መከበሩ የፈጠረውን ደስታ በወጉ አጣጥመን ሳንጨረስ ለአገር ግንባታ የሚኖረውን አውንታዊ አስተዋጾ አስልተን ሳናበቃ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዛኔው ምክትል ርዕሰ መስተዳደር አቦ ሽመልስ አብዲሳ ሳቱት የተባለው የፖለቲካዊ ትክክለኝነት ኢላማ ቀደም ሲል ከተፈጠሩ ፖለቲካዊ ኢትክክለኝነቶች ጋር ተዳውሮ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የኖቤል የሰላም ተሸላሚ መሆናቸው የፈጠረብንን ሀሴት በቅጡ ሳናጣጥም አዲስ አበባ ላይ የተቃውሞ ሰለፍ መጠራቱ የችግሩን አሳሳቢነት ያሳያል። ከእያንዳንዱ ፖለቲካዊ ኢትክክለኝነት ጀርባ የሚከፋ፣ የሚያኮርፍ፣ የተገለለ፣ ኢላማ የተደረገ የሚመስለው የሕብረተሰብ ክፍል መኖሩን ለምን በተደጋጋሚ እንደምዘነጋ ሁልጊዜ እንቆቅልሽ ይሆንብኛል።

ሆኖም የአገራችንም ሆነ የውጭ አንዳንድ ልሒቃን ፖለቲካዊ ትክክለኝነትን የንግግርና የሀሳብ ነፃነትን እንደሚገድብ ያወሳሉ ። የሜሪ ላንድ ዩኒቨርሲቲው ዳን ሞለር ፖለቲካዊ ትክክለኝነት የንግግር ነፃነት የመገደብ ጉዳይ ሳይሆን ነፃነቱ የሌላውን መብት፣ ባህል፣ ታሪክ፣ ማንነት፣ ወዘተ . በማይነካ፣ በማያንቋሽሽና በማይሸረሽር መንገድ የመጠቀም አግባብ ነው ሲሉ ይሞግታሉ ። አላማውም :-

1ኛ . ተጋላጭ፣ ተገላይ እና በታሪክ አጋጣሚ ተጠቂ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን መከላከል።

2ኛ . ሕዝቡ የሚወያይባቸው፣ የሚነጋገርባቸው ርዕሰ ጉዳዮችን በማረቅ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠቂ እንዳይሆኑ መስራት ።

3ኛ . በዜጎች መካከል ቁጣን፣ ግጭትን፣ ጥላቻን የሚቀሰቅሱ ንግግሮችን መከላከል መሆኑን ያሳያሉ።

ይሁን እንጂ ዳን ቀለል ባለ ምሳሌ ሲያስረዱ አንድን የሕብረተሰብ ክፍል ዝቅ የሚያደርግ የታሪክ የመማሪያ መፅሐፍት እንዲታረም መጠየቅ የፖለቲካዊ ትክክለኝነት ጉዳይ ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም ።

እንደ ታዋቂው የኢኮኖሚክስ ባለሙያ ግሌን ሎሪ ያሉም ፖለቲካዊ ትክክለኝነትን ሀሳብን የመግለፅና የንግግር ነፃነትን እንደሚገድብ አድርገው የሚወስዱ አሉ። ሎሪ ፖለቲካዊ ትክክለኝነት የሚቃወሙበት ሌላው መከራከሪያ ራስን መመርመር ማቀብ ( self censorship ) ያስከትላል በሚል ነው። የጀርመኑ (ፖለቲከኛ ፊሊፕ ጄኒንገር ስለናዚ ዘመን ጀርመናውያን በማውራቱ ብቻ የናዚ ደጋፊ ወይም ፀረ ፂወናዊ እንዳልሆነ እየታወቀ በመናገሩ ብቻ ከፖለቲካ ሕይወቱ እንዲገለል ተደርጓል። የውሾን ነገር ያነሳ ውሾ በሚል መሆኑ ነው። የዋሽንግተን ከንቲባ ሹመኛም በአንድ ወቅት ጓደኞችን "niggardly " (ቆንቋኖች) ብሎ መሳደቡ ቁጣ በመቀስቀሱ ከኃላፊነቱ በገዛ ፈቃዱ ለመልቀቅ ተገዷል። ከዚህ ከዚህ አንፃር ፖለቲካዊ ትክክለኝነትን ስንመዝነው ለምዕራባውያን ለቅንጦት የቀረበ ሊመስል ይችላል እንደኛ በለውጥ በሽግግር ላይ ላለ አገር ግን የህልውና እንዲሁም የሞት ሽረት ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል። በተለይ አመራሩ ብርቱ ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል። አንዱ ራሱን በሌላው ጫማ አድርጎ ማየት ያሻል። ኦሮሞ ብልጽግና ራሱን በአማራ ብልጽግና ጫማ ፤ የአማራም እንዲሁ ማድረግ ይጠበቅበታል ።

### እንደ መውጫ

በአገራችን ፖለቲካዊ ትክክለኝነትን በማበረታታት ረገድ ገዥው ፓርቲ ብልጽግና የአንበሳውን ድርሻ እና ቀድሞ ተነሳሽነቱን በመውሰድ አርዓያ ሊሆን ይገባል። በፓርቲው ሕገ ደንብ ላይ በማያሻማና ግልፅ በሆነ ቋንቋ ስለፖለቲካዊ ትክክለኝነት አስፈላጊነት ሊደነግግ በቀጣይም ለአባላቱና ለደጋፊዎችም የግንዛቤ ማስጨበጫ ተከታታይ መድረኮችን ሊያዘጋጅ ይገባል። በየደረጃው ያሉ የፓርቲው አመራሮች የሚገዙበት የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም የስነ ምግባር መመሪያ ሊኖረው ይገባል። ይህን በሚተላለፉ አመራሮች ላይም አስተማሪና መቀጣጫ ሊሆን የሚችል እርምጃ ሊወስድ ይገባል።

በከፍተኛ ትምህርትም ሆነ በሌሎች ተቋማት የሚገኙ ልሒቃን በፖለቲካዊ ትክክለኝነትን ምንነትና አስፈላጊነት ላይ ሀሳብ በመለዋወጥና ችግሩን ከእነ መፍትሔው በማመላከት የዜግነት ግዴታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል። ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችም የድርሻቸውን ከመወጣት ባሻገር የፖለቲካዊ ትክክለኝነት ጥያቄን የሚያስነሱ ጉዳዮችን በመለየት መሪዎቻቸው በመግለጫዎቻቸው በንግግሮቻቸው በቅስቀሳቸው ፖለቲካዊ ትክክለኝነትን ታሳቢ እንዲያደርጉ አባሎቻቸውና ደጋፊዎቻቸውም ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባል።

ሚዲያው በአርትኦት ፖሊሲው ፖለቲካዊ ትክክለኝነትን በማካተት ኃላፊነቱን ለመወጣት አበክሮ መስራት ይጠበቅበታል ።

እንደ ዜጋ ደግሞ ሁላችንም የምንፅፈው፣ የምንናገረው፣ የምንስለው፣ የምናዜመው፣ የምንቀርፀው፣ ወዘተረፈ የሌላውን ወገን ታሪክ፣ ባህል፣ እሴት፣ ሃይማኖት፣ ማንነት፣ ወዘተ . የመያናንቅ፣ የማያንኳስስ እንዲሁም በሌላው ቁስል ላይ እንጨት የማይሰድ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባናል።

የሰለጠነ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ እስክንጨብጥ፤ የዴሞክራሲያዊ ተቋማት በአግባቡ እስኪጎለብቱ፤ በመንግስት አካላት ማለትም በሕግ አውጭው፣ ተርጓሚውና አስፈፃሚው መካከል ያለው ግንኙነት ሚዛናው እስኪሆን ፖለቲካዊ ትክክለኝነትን የሙጥኝ ብሎ መያዝ ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም። ስንከተለው የነበረ አገዛዝ ያመጣብን መለያየትና መጠራጠር ሳያንስ በፖለቲካዊ ኢትክክለኝነት አገር ልትታመስ ሕዝብም ሊደናገር አይገባም ።

ፖለቲካዊ ትክክለኝነት አሁኑኑ ! ! !

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

# ከተኪ ምርቶች እስከ ሰለጠነ የሰው ሀይል ማምረት

ፍሬህይወት አወቀና አሥመረት ብሥራት

ከአነስተኛና ጥቃቅን ስራዎች ተነስተው ወደ መካከለኛ ብሎም ከፍተኛ አቅም ያላቸው ኢንቨስተሮችን ለመፍጠር የተለያዩ ማኑፋክቸሪንጎች ተቋቁመው ወደ ስራ ከገቡ አመታት ተቆጥረዋል። በዚህም ለበርካቶች የስራ እድል ከመፈጠሩም ባሻገር ለአገር ኢኮኖሚም የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እያደረጉ መሆኑ ይታወቃል። በርካቶች ስኬታማ ሆነው የእድገት ደረጃቸውን ጠብቀው እየተጓዙም ቢሆንም ጥቂት የማይባሉቱ ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ኋላ ቀርተው እንመለከታለን።

ተሳክቶላቸው ለአመታት በስራው ላይ የቆዩት የያሬድ ብረታ ብረትና እስፔር ፓርት ማሽነሪ ማምረቻ ስራ አስኪያጅ አቶ ያሬድ እስጢፋኖስ ራሳቸውን ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ ካሳደጉት መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። በአሁኑ ወቅት ትላልቅ የሚባሉ ዘመናዊ ማሽኖች በማምረትና በስፋት በማከፋፈል ላይ ናቸው። የግል ጥረታቸው ከመንግስት ድጋፍ ጋር ተዳምሮ ስኬታማ ለመሆን በቅተዋል። ለብዙዎች እንጀራ ከመከፈት በተጨማሪ ለነገ የሚሆናቸው የሙያ ባለቤት ጭምር አድርገዋል። እዚህ ደረጃ የደረሱት ግን ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ሆኖላቸው አይደለም። እርሳቸውም ስራው ፈታኝ ቢሆንም የስራው ፍቅር በዚህ ዘርፍ እንዳቆያቸው ይናገራሉ። ወደ ስራው የገቡት በ2003 ዓ.ም ሲሆን ፋብሪካቸው ከመቋቋሙ ቀደም ሲል በመኪና ጥገና ስራ ላይ ተሰማርተው እንደነበር ያስታውሳሉ። ወደዚህ ስራ ለመግባት ያነሳሳቸው የቀድሞ ስራቸው መሆኑን የሚናገሩት አቶ ያሬድ በአገሪቱ የሚነዱ መኪኖች የምርት ዘመናቸው ከመቆየቱ የተነሳ መለዋወጫ የማይገኝላቸው ሲሆኑ ለምን ለእነዚህ መኪኖች የሚሆኑ መለዋወጫዎችን በራሳችን አናመርትም በሚል መነሻ ድርጅታቸውን መክፈታቸውን ይናገራሉ።

አስመስለው የተሰሩ (ሞዲፊክ) የመኪና መለዋወጫዎችን በመስራት ችግርን በአገር ውስጥ ምርት ለማቃለል በሚል የተጀመረው ስራ ሙሉ ለሙሉ መለዋወጫዎችን ወደማምረት ስራ ካደገ በኋላ ለስምንት አመታት ከውጭ የሚመጡ የተለያዩ ማንኛውም አይነት ማሽነሪዎች፣ የአዳራሽ ወንበሮች፣ የመኪና መለዋወጫ እቃዎችን ያመርታሉ።

የተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት ማለትም እንደ ደቡብ ግሎባል ባንክ አይነቶቹ፣ የተለያዩ በእቃው መጠቀም የፈለጉ ግለሰቦች፣ የአዳራሽ ወንበር የሚፈልጉ ተቋማት ደንበኞቻቸው መሆናቸውን የሚናገሩት አቶ ያሬድ ለምሳሌ የዳቦ ማሽኖች፣ የእህል ወፍጮዎች፣ የሳሙና ማምረቻ፣ የወርቅ ማጠቢያ ማሽኖች፣ ትናንሽ የቤት ውስጥ መገልገያ የዳቦ መጋገሪያዎች፣ ቡና ማድረቂያ፣ ቆሎ መቁያ፣ ቡና መፍጫ በአጠቀላይ ደንበኞች ለሚፈልጉት ግልጋሎት ሊያውሉት የሚችሉት ማንኛውም ማሽን የማምረት ስራ የሚሰራ መሆኑን ያስረዳሉ።

“የእያንዳንዱ ስራ ትእዛዝን ስንቀበል የደንበኛውን ፍላጎት በመረዳት በጥንቃቄ ዲዛይን ተደርጎ ወደ ምርት ይገባል።” የሚሉት አቶ ያሬድ ከሁሉም በላይ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ ለመተካት የሚያስችል ምርቶችን በብዛትም ሆነ በተናጠል ለሚያዙ ደንበኞች እንደየ ፍላጎታቸው አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን ይናገራሉ።

ማሽኖቹን ለመስራት የተለያዩ ጥሬ እቃዎችን ይጠቀማሉ። እንደ ብረት፣ አለሙኒየም፣ እንጨትና የተለያዩ ለማሽን መስሪያ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ተጠቅመው ያመርታሉ። አዳዲስ ጥሬ እቃዎችን ከመጠቀመም በላይ የማይፈለጉ ተብለው የወዳደቁ ብረታ ብረቶችን እንደ አዲስ በማቅለጥ ግልጋሎት ላይ የሚያውሉ መሆኑን ይናገራሉ። የወዳደቁ እቃዎችን፣ የአገልግሎት ዘመናቸውን የጨረሱ የመኪና መለዋወጫዎች፣ ከየአካባቢው የወዳደቁና ቁርጥራጭ ከሚሰበስቡ ብረቶች፣ ተረፈ ምርቶችን በኪሎ በመግዛት አንድ ላይ በመሆን የሚያቀልጡ ሲሆን ሞልድ በማዘጋጀት ወደ ተፈለገው ማቴሪያል የሚቀየር መሆኑን አቶ ያሬድ ያስረዳሉ።

ሀዋሳ ከተማ ተወልደው ያደጉት አቶ ያሬድ በፈጠራ ላይ የተመሰረተውን ድርጅታቸውን ከመክፈታቸው በፊት በአውቶሞቲቭ የትምህርት ዘርፍ ስልጠናን ወስደዋል። ለረጅም አመታት በፍቅር የቆዩበት ሞያም በመሆኑ ክፍተቶቹን እየተመለከቱ ስራ ፈጣሪ ለመሆን መቻላቸውን ይገልጻሉ። የመኪና ጥገና ስራ ላይ ይህ ቀረሽ የማይባሉ ባለሞያ መሆናቸውን የሚናገሩት አቶ ያሬድ በመኪና ስራ ላይ ከኤሌክትሪክ እስከ ሞተር፣ ከሞተር እስከ ቦዲ ስራ እያንዳንዱን ነገር የሚሰሩ መሆኑን አብራርተዋል።

“ስፈጠር ጀምሮ ለፈጠራ ስራ ነው “ የሚሉት አቶ ያሬድ ከልጅነት ጊዜያቸው ጀምሮ የተለያዩ ነገሮችን መሞከር ያስደስታቸው እንደነበር ይናገራሉ። አንድ ነገር ሲመለከቱ ከዚህ በተሻለ እንዴት አድርጌ ልሰራው እችላለሁ የሚል ሀሳብ በውስጣቸው እንደሚፈጠር የሚናገሩት አቶ ያሬድ ህይወትን ቀለል ለማድረግ የሚያስችሉ በተለይም ከውጭ በውድና በውጪ ምንዛሬ ወደ አገር ቤት የሚገቡ ቁሳቁሶችን ለመተካት ማሰብ ሀሳብን ደግሞ ወደተግባር ከዚያም ወደስኬት መቀየር የዘወትር ስራቸው እንደነበር ያስታውሳሉ።

አሁን በተኪ ምርቶች ላይ ትኩረት ቢያደርጉም በቀጣይ በኤክስፖርት እስታንዳርድ በማምረት ምርቶችን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እቅድ አላቸው። ሆኖም ግን አሁን ካለው የአገሪቱ ሁኔታ አንፃር የገንዘብ አቅም ማነቆ እንደሆነባቸው ያስረዳሉ። የአቅም ውስንነት ባይኖር ግን በፍጥነት የተለያዩ ምርቶችን በማምረት ወደ ውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚሰሩ መሆኑን ገልፀዋል። በድርጅቱ ከውጭ የሚገቡ እቃዎችን በመተካት የውጭ ምንዛሪን የማስቀረት ስራን ከመስረታቸው ባሻገር አሁን ደግሞ የውጭ ምንዛሪ በማምጣት የአገሪቱን ኢኮኖሚ ለመደገፍ የሚሰሩበትን ሁኔታ ማቀዳቸውን ያስረዳሉ።

ምርቶችን የማምረት ሂደት ውስጥ አንድ አይነት አካሄድ ብቻ እንደማይከተሉ የሚናገሩት አቶ ያሬድ፣ በርከት ያሉ ትእዛዞች ወደ ድርጅቱ ሲመጡ ሌሎች በአካባቢው ያሉና በሙያው ብቁ ለሆኑ አጋር ድርጅቶች የተለያዩ ክፍሎችን ድርጅቱ በሚፈልግው የጥራት ደረጃ መሰረት ጥሬ እቃ በማቅረብ እንዲሰሩ የሚደረግበት አግባብ መኖሩን ገልፀዋል። ስራውን የተቀበሉት አካላት የእውቀታቸውንና የማሽናቸውን በቂ ክፍያ የሚያገኙ ሲሆን ድርጅታቸው በስራ ብዛት እንዳይጨነቅ ያደርጋል። ይህን ከማድረጉም ባሻገር በአካባቢው በርካታ የበቁ ሞያተኞች እንዲኖሩ እድል የሚሰጥ መሆኑን ያብራራሉ።

በስራ እድል ፈጠራ ረገድ በድርጅቱ የሚሰሩ ሀምሳ አራት ሰራተኞች መኖራቸውን ገልፀው ስራው በሚፈለገው መልኩ ቢገኝ ከዚህ ተጨማሪ የሰው ሀይል ለመቅጠር ያስባሉ። ስራ በአግባቡ ላለመገኘቱ እንደማነቆ የሚያነሱት ስራ ለመስራት ጨረታዎች ሲወጡ ለሚፈለገው ሰው ብቻ ለመስጠት አጥር የሚቀመጥበት አሰራር መኖሩን ነው። ይህም ሁሉም አምራች በተገቢው መልኩ ተወዳዳሪ እንዳይሆን እንዳደረገው ያስረዳሉ። ለዚህም መፍትሄ ነው ያሉት ሀሳብ የመወዳደሪያ ሜዳውን እኩል ክፍት በማድረግ በማደግ ላይ ያሉ ኢንዱስትሪዎችን ማበረታታት የግድ መሆኑን ያስረዳሉ።

“መንግስት ማኑፋክቸሪንጎች ይደጉ ካለ፣ ምርቶቻችን የውጭ ምንዛሪ ማስቀረት ከቻለ፣ ለአገር ኢኮኖሚ ደጋፊ ስራ መስራት ከቻልን ሙሉ አቅማችንን የምንጠቀምበት አሰራር መዘርጋት አለበት” የሚሉት አቶ ያሬድ ስራው በተጀመረበት ልክ መሄድ እንዲችል ሰራተኞች እንዳይበተኑ መንግስት ድጋፉን እኩል ማድረግ የሚገባው መሆኑን አሳስበዋል።

አቶ ያሬድ እንደሚሉት፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ጥራት ያለው እቃ በአገር ውስጥ ማምረት እየቻሉ በጣም በቀላሉ ሊመረቱ የሚችሉ እቃዎችን ከውጭ የማስመጣት ፍላጎት በመንግስት ተቋማት መኖሩ አሳሳቢ ነው። መንግስት የስራ እድሎችን መፍጠር የስራ አጥ ቁጥር መቀነስ የሚሉ ሀሳቦችን እያነሳ ስራ ውስጥ ያሉ አካላት አቅም ሳያንሳቸው በገበያ እጦት የተነሳ ስራ እንዳይቆሙ ማድረግ እንዳለበት ይናገራሉ። ይህም ሲባል አምራቾች ተገቢው የጥራት ደረጃ ተቀምጦላቸው ጥራቱ ከውጭ ከሚመጡት ጋር በማወዳደር ቅድሚያ ለአገር ውስጥ አምራቾች መስጠት ይበልጥ ኢንዱስትሪውን ለማሳደግ የራሱን አስተዋፅኦ ይኖረዋል።



አቶ ያሬድ እስጢፋኖስ

ማምረት መሸጥ ከሚለው እሳቤ ባሻገር እውቀት ያላቸው ሙያተኞችን በማፍራት ረገድ የራሳቸውን ድርሻ እየተወጡ መሆኑን የሚናገሩት አቶ ያሬድ፣ በድርጅታቸው ስልጠና ከመስጠቱ ባሻገር አሁን ላይ ስርዓተ ትምህርት በማስቀረፅ የቴክኖሎጂ ስልጠናዎች ባደራጁት ኮሌጅ ውስጥ እስከ ድግሪ ደረጃ የሚደርስ ስልጠና እየሰጡ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የፅንሰ ሀሳብ ትምህርትን በኮሌጅ ከተማሩ በኋላ ልምምዳቸውን በወርክ ሾፑ በመስጠት ምርቱን ለገበያ የሚያቀርቡ ሲሆን ተማሪዎቹም ልምድ ካለው ባለሙያ ጋር በመጣመር በተግባር የተደገፈ ትምህርት በማግኘት ብቁ የሰው ሀይል የማፍራት ስራ ላይ መሰማራታቸውን ያስረዳሉ።

በኮሌጁ ለጊዜው ወደ አንድ መቶ ሰማኒያ አካባቢ የድግሪ ተማሪዎች ያሉ ሲሆን የመጀመሪያ ድግሪ ተማሪዎች በኮሌጁ አራት አመታትን ይቆያሉ። ይህ ሲባል ግን በክፍል ውስጥ አመት ከቆዩ በኋላ እጅ ከማፍታታ ጀምሮ ብቁ ባለሙያ እስኪሆኑ ድረስ በወርክ ሾፕ ውስጥ የሚቆዩ ሲሆን ስልጠናው 30 በመቶ በንድፈ ሀሳብ 70 በመቶው የተግባር ሆኖ ይጠናቀቃል ብለዋል።

የሙያ ስልጠና በድግሪ ደረጃ የሚያስተምር በደቡብ ክልል ብቸኛው ተቋም መሆኑን ገልፀው በኮሌጁ የሚሰጡት የስልጠና ዘርፎች አውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ፣ ኤሌክትሮኒክስ ቴክኖሎጂ፣ ሜታል ፋብርኬሽን፣ ማሽን ቴክኖሎጂ፣ የትምህርት ዘርፎች መሆናቸውን ተናግረዋል። ከእነዚህም መካከል አውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ፣ ኤሌክትሮኒክስ ቴክኖሎጂ፣ በድግሪ ደረጃ የሚሰጥ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ በሌቭል ደረጃ የሚሰጡ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

ቀደም ሲል ዲፕሎማ ይዘው በድርጅቶችና በተለያዩ ቦታዎች ተቀጥረው የነበሩ የሞያ ብቃታቸውን መሻሻል ሳይችሉ ቀርተው ተቸግረው የነበሩ በርካታ ሰዎች ትምህርታቸውን ከፍ ለማድረግ ከሚኖሩበት ሀዋሳ የግድ መልቀቅ ነበረባቸው የሚሉት አቶ ያሬድ፣ አሁን ግን በአካባቢው ላለው ማህበረሰብ የትምህርት ፍላጎትን ሊያሟላ የሚችል ኮሌጅ በአቅራቢያው ለመክፈት መቻሉ መማር ለሚፈልጉ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል።

በማህበራዊ አገልግሎት ረገድ የሰው ሃይል ማምረት ከማህበራዊ አገልግሎቱ አንዱ ሲሆን፣ በዚህም በማሰልጠኛ ኮሌጁ ውስጥ ነፃ የትምህርት እድል ለዘጠኝ ልጆች መስጠቱን ነው የገለጹልን። አገራዊ ጥሪዎችም ሲኖሩ በንቃት በመሳተፍ አገልግሎት የመስጠት ሀላፊነታቸውን እየተወጡ መሆኑንም ተናግረዋል።

ቀደም ሲል በጥቃቅንና አነስተኛ ደረጃ ሲሰሩ ቆይተው ወደ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ደረጃ ሲያድጉ መንግስት የተለያዩ ድጋፎችን እንዳደረገላቸው ይናገራሉ። ከዚህም ውስጥ 800 ካሬ ሜትር የማምረቻ ቦታ የተሰጣቸው ሲሆን ምርቶቻቸውን ለማሳየት የሚያስችል አዳራሽ ተከራይተዋል። በቀጣይም ከፍተኛ ደረጃ ለመድረስም ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ይናገራሉ። በቀጣይ ስራው ሲሰፋ የፕላስቲክ ምርቶችን እስፖንጅና ሌሎችን ለመስራት የሚያስቡ ሲሆን ለዚህም የሚሆን የስራ ትስስሩ ላይ ትኩረት ቢደረግ ውጤታማ ያደርገናል ይላሉ።

“ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መር መሸጋገር አለብን ሲባል በተደጋጋሚ ጊዜ ይነገራል። ይሄንን ከወሬ ባለፈ በተግባር ማየት ብንችል፣ የፋይናንስ አቅርቦት ላይ በቂ የብድሮች ሁኔታዎች ቢመቻቹ፣ ስራውን የምናሳድግበት ከዛም አልፎ እኩል የመወዳደሪያ ሜዳ ቢኖር ስራውን ለማሳደግ ምንም እንደማይከለክለን አስባለሁ” ይላሉ።

ብልሹ አሰራሮችን በማጥራት ሰው በሙያው ብቻ መመዘን ቢችል የተፈለገውን ያህል ውጤት ማምጣት የሚቻል መሆኑን ይናገራሉ። በአጠቃላይ በስራቸው ውጤታማ የስራ ፈጣሪዎችን በማበረታታት የተሻለ ስራዎችን እንዲሰሩ ድጋፍ ቢደርግላቸው መልካም መሆኑን አንስተዋል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ጎሜ

# እህህ .... አስ ፈረስ

**ሙሉቀን ታደገ**

ወፈፌው ይልቃል አዲሴ፣ የእድራችን መሪ አቶ አህመድ ይመርን በክርክር ከረታ ወዲህ እንደዚህ ቀደሙ በየቀኑ ሌሊት እየተነሳ መጮሁን አቁሟል። ወትሮ ሰማይ የአህያ ሆድ ሲመስል መጮህ የጀመረ ማታ የሌሊት ወፎች ከዋሻቸው ወጥተው ውር ውር ማለት ሲጀምሩ ነበር የሚያቆመው። አሁን ላይ ግን በክርክሩ የእድራችንን መሪ ካሸነፈ በኋላ እንኳንስ ቀኑን ሙሉ ሊጮህ ይቅርና እሁድ እሁድ እንኳን ለሰፋራችን ሰዎች መልዕክት ለማስተላለፍ ሲፈልግ ብቻ ነው የሚገኘው። ጩኸቱም እንደዚህ ቀደሙ በወፈፌነት የሚታለፍ አይደለም። ሁሉም የእድራችን እና የሰፈራችን ሰዎች በጥሞና እየተከታተሉ በጭብጨባም ያጅቡታል እንጂ።

የዛሬው የይልቃል አዲሴ የዋርካው ስር ንግግር ትንሽ ጠጠር ያለ እና በምሳሌዎች የታጀበ ነበር። የዛሬ ንግግሩን የጀመረውም በእርሱ መምጣት የተደሰቱ ሰዎችን በመገሰጽ ነው። የሰፈሩ ሰዎች በይልቃል አዲሴ መምጣት ተደስተው ሲያጨብጭቡ፤ ምን የሚያስጨበጭብ ነገር አለና ነው የምታጨበጭቡት! ? ሲል ንግግሩን ጀመረ።

ንግግሩን ቀጠሎም.....ዛሬም ካለፈው ስህተታችሁ አትማሩም ? ባለፈው ጊዜም ለእድራችን እና ለሰፈራችን መሪ እንዲሁም አላዋቂዎች ለሆኑ ተፎካካሪ ሃይሎች በሆነ ባልሆነው እጃችሁ እስኪላጥ አጨብጭባችሁ አጨብጭባችሁ አላዋቂዎችን እንዲታወቁ አደረጋችሁ። ሳያውቁ እንዲታወቁ የተደረጉት ኃይሎች ከማንም በላይ ያወቁ መስሏቸው ራሳቸውን በግብዝነት ቆለሉ። እነኝህ አላዋቂዎችም ከእድራችን ህግ እና መርህ ውጭ ለራሳቸው በመሰላቸው መንገድ ነገሮችን እየሰፉ እና እየቀደዱ ሰፈራችን እና እድራችንን እንዳልሆነ አድርገው እየበጠበጡት ነው።

በእነኝህ ሰዎች ሰበብ ሰፈራችን እና እድራችን ለመበጥበጡ ከእነሱ በላይ ተጠያቂዎች እኛ ነን። ምክንያቱም ሳያውቁ እያጨበጨብን እንዲታወቁ ያደረግናቸው እኛ ስለሆንን። ዛሬ ለእኔ እዳጨበጨባችሁት ሁሉ በዚያን ጊዜም ለግብዞቹ ዝም ብላችሁ ስታጨብጭቡ ምን ብያችሁ ነበር....? ወፈፌ ተብየ ሰሚ አጣሁ እንጂ።

ያኔ እኔን ወፈፌ ስትሉኝ ደስተኛ ነበርኩ። ምክንያቱም በእኛ ሰፈር ከወፈፌዎች፣ ከእድር መሪዎች እና ተፎካካሪ ኃይሎች በቀር እንደልባቸው እንዲናገሩ ለማንስ ይፈቀዳል? ይሄን በወፈፌነት ስም እንደፈለጉ መናገርን ማንስ ሊታደል ይችላል? እኔን ወፈፌ ብላችሁ ስትፈርጁኝ ደስ ብሎኝ ነው የተቀበልኳችሁ።

በአንጻሩ ግን ሲያስነጥሱም ሳይቀር ስታጨበጭቡላቸው የነበሩ በተለይም እድራችንን ለመምራት የሚፎካከሩ ሃይሎች በእናንተ ጭብጨባ የተነሳ ከሚችሉት በላይ ሃላፊነት አሸከማችኋቸው። እነኝህ ከአቅማቸው በላይ ሃላፊነትን የወሰዱ ሰዎችም በእድራችን ህግ እና ስርዓት መመራትን እንደ ነውር እየቆጠሩ በየጎጣቸው ራሳቸውን የጎበዝ አለቃ እያደረጉ ሾሙ። የእድራችን መሪ ስለምን ይህን ታደርጋላችሁ? ቢላቸው ምን አገባህ! ሲሉ መለሱ። እነኝህ ሃይሎች ከእድር መሪያችን ህግን እንዲያከብሩ ማስጠንቀቂያ በተሰጣቸው ቁጥር እንወክለዋለን የሚሉትን ጎሳ ጥፋት ታውጆብሃል እያሉ ለጥፋት በማስነሳት እድራችን እና ሰፋራችንን ሲያበጣብጡ ይሄው ድፍን አራት አመት ተቆጠረ።

ራሳቸውን እንደ ጎበዝ አለቃ በሚቆጥሩ ኃይሎች ተገርመን ሳንጨርስ ሰፈራችንን እና እድራችን እንዲያስተዳድሩ ስልጣን የተሰጣቸው ሰዎች እርስ በርስ በጎጥ ይነታረኩ ይዘዋል። ከሁሉም የሚያስገርመው ደግሞ የእነሱ ንትርክ ነው። ስልጣን ይዘውም ይነታረካሉ? ያኔ የለውጡ ሰሞን በተለይ በእድራችን ውስጥ የሚገኙ መደበኛም ሆኑ ኢመደበኛ ጡሩምባ ነፊዎች እኔን ወፈፌ እያሉ ሲሳደቡ እና ሲያብጠለጥሉ አላዋቂዎችን ደግሞ ሲያሞካሹ ስመለከት ይች ቀን እንደምትመጣ እርግጠኛ ነበርኩ። ለማንኛውም ዛሬም አረፈደም፤ ከዚህ በኋላ ነገሮችን በስሜት ከመወሰናችሁ በፊት፡-

"አስበን እንስራ ስነገም እንዲሆን፤
ይሁን ይሁን ብለን የማይሆን እንዳይሆን፤"

የሚለውን የአንዳርጌ መስፍን ግጥም ደጋግማችሁ፣ ደጋግማችሁ እንድታስቡት እሻለሁ፤ ሲል ትዕዛዝም ማሳሰቢያም አክሎ ነገራቸው።

ይልቃል ንግሩን ቀጠለ፤ ......ፈረስ እህህህ .... ማለቱ ሁኔታዎች ቢያስገርሙት አይደል! ፈረስ ስል በሰፈራችን የነበረን አንድ ፈረስ አስታወስኩ። በሰፈራችን በባለቤቱ ይጨቆን የነበረ ፈረስ ነበር። መጨቆኑ ያንገበገበው ፈረስ ከዕለታት በአንድ ቀን የት ገባ ሳይባል ከቤቱ ይጠፋል። እንደጠፋ ሳይመለስ በዚያው ያድራል። ውጭ ባደረ ጊዜም ያገኘውን ሰብል ያለማንም ከልካይ እንደልቡ ሲበላ ያድራል። ሆዱም ያለመጠን ይጠግባል። ቁንጣንም የሚይዘውን ሚጨብጠውን ያሳጣዋል። በዚህም ሳቢያ አነጋጉ ላይ አቶ ፈረስ ባገኘው ቦታ ላይ ተዘራግቶ ይተኛል። ይህ በእንዲህ እዳለ በጠዋት ምግባቸውን ለመፈለግ የተነሱ ጥንብአንሳ አሞራዎች ከላይ ወደታች ሲመለከቱ አንድ ፈረስ መሬት ላይ ተዘርሮ ያያሉ። አቶ ፈረስም በጣም ጠግቦ ስለነበር ምንም አይነት እንቅስቃሴ አያደርግም ነበር።

ይህን የተመለከቱ አሞራዎች ፈረሱ የሞተ ይመስላቸዋል። በጠዋቱ ብዙ ሳንለፋ ቀናን ብለው ወደ ተዘረረው ፈረስ ተጠጉ። ፈረሱ የሞተ የመሰላቸው አሞራዎች በቁንጣን ያበደውን ፈረስ ለመብላት ቋምጠው በፍጥነት በምንቋራቸው አቶ ፈረስን ውግት ....ውግት ማድረግ ይጀምራሉ። በዚህ ጊዜ የአሞራዎች ንክሻ ያመመው ፈረስ አይኑን ገለጥ አድርጎ ሲመለከት አሞራዎች ከበውታል። በምንቋራቸውም እየወጉት ነው። በዚህ ጊዜ በቁንጣን መሬት ላይ የተዘረረው ፈረስ አንገቱን ብቻ ቀና አድርጎ በንዴት ምን እያደረጋችሁ ነው!? ሲል አሞራዎችን ጠየቃቸው። አሞራዎችም ያልጠበቁት ነገር ስለገጠማቸው ተደናግጠው «ታመህል ተብሎ ልንጠይቅ» አሉት። ፈረሱም አሞራዎች ለምን እንደተሰባሰቡ ስለገባው «እህህህ .....» አለ ይባላል። ከዚያ በኋላም የፈረሰ ጩኸት እህህህ ሆኖ ቀረ።

እኔ እና የሰፈራችን ሰዎችም ለዘመናት በጭቆና ወድቀን በመኖራችን እና ለውጡን ተከትሎ ከችግር እና ከመከራ ተላቀቅን እፎይ ልንል ነው ብለን በደስታ ቁንጣን ሰክረን በተኛንበት ስለምን የእድር መሪዎቻችን እና ተፎካካሪ ሃይሎች እኛን በጎሳ ስም እየከፋፉሉ ሊያጠፉን እንደፈለጉ ስለገባን እንደ አቶ ፈረስ እህህ ብለናል!

ቅቤን ወተት ማድረግ አይቻልም። ወተትን መጠጣት የሚፈልግ ሰው ወተቱን በጊዜ መጠጣት ይኖርበታል። ጊዜው አልፎ ወተት ወደ ቅቤ ከተቀየረ በኋላ ቅቤን ወተት ላድርግ ቢሉ የማይቻል እና የማይሞከር ነው ትርፉ ድካም ነው ። አሁን ላይ የእድራችን መሪዎች እና እድራችንን ለመምራት የምትራኮቱ ሃይሎች ወተቱን መጠጣት ከፈለጋችሁ በወተትነቱ መጠጣት ተገቢ ነው። ነገር ግን ወተቱ እረግቶ እና ተንጦ ወደ ቅቤነት ከተቀየረ በኋላ ቅቤውን ወተት አድርጉ ብሎ የሰፋራችንን እና እድራችንን ሰዎችን ማስቸገር አግባብነት ለውም። ከአሁን በኋላ እንደዚህ አይነቱን ግብዝነት የምንታገስበት ትከሻ የለንም።

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት የነበረው ዋረን ሃርዲንግ «ተገቢ ለሆነ ምክንያትም እንኳን ቢሆን ህሊናን የሚወቅስ ስራ አትስራ» ይሉ ነበር። እውነት ነው! የእኛ መሪዎች እና ተፎካካሪዎች ግን ተገቢነት ለሌለው እና ህሊናን የሚያቆስል፤ ቅቤን መልሳችሁ ወተት አድርጉ አይነት ትዕዛዝ እያስተላለፉ የሰፋራችንን ሰዎች በጎሳ በመከፋፈል ለማጣላት ሲጥሩ ይታያል፤ ይሄ እኮ በእነሱ ቤት ፖለቲካ መሆኑ ነው ? ድንቄም ፖለቲካ...!

ታላቁ የቻይና ፈላስፋ ኮንፊሼስ "በራስህ ላይ ሊደረግብህ የማትፈልገውን በሌላ ላይ አታደርግ። "ይላል። እናንተ አቅልላችሁን በክፋት እና በጥፋት የተሳተፋችሁ የእድራችን መሪዎችና ተፎካካሪዎች ምን አለበት በእናንተ ላይ ሊፈጽምባችሁ የማትፈልጉትን በጥላቻ እና በቅናት ጠርዝ ላይ ቆማችሁ በወንድም እና በእህቶቻችሁ ላይ ባትፈጽሙ?

የጤና ሚንስትራችን ፎቶ ያሉበት በአንበሳ አውቶብስ ማቆሚያ ቦታዎች ላይ የሚገኝ አንድ ቀልቤን የሳበኝ አባባል አለ። «የወገኔ ጤነኝነት ያሳሳስበኛል.. » የሚል። ይህን አባባል ስመለከት የጤና ሚንስትሯ የእድራችን መሪዎችን እና ተፎካካሪ ሃይሎችን ተመልክተው የተናገሩት ንግግር መስሎኝ ተግርሜአለሁ። ለነገሩ አያስገርምም!... ስለወገናችን ጤነኝነት ከጤና ሚንስትራችን በላይ ማን ሊያውቅ ይችላልና?

በሰፈራችን እና በእድራችን እየተፈጠረ ያለው ችግር ለመሪዎቻችን እና ለተፎካከሪዎች የወደዱት ይመስላል። ሰው መጥፊያውን እንዴት ሊወድ ይችላል? ይህን ስል አንድ ነገር ትዝ አለኝ። ልጅ እያለሁ በሰፋራችን በስካሩ የሚታወቅ አቶ ፈጠነ የሚባል ሰው ነበር። አቶ ፈጠነ፣ ከአጎቴ ማህበር ተጠርቶ መጣ። ከመጠን በላይም ጠጣ። ከመጠን በላይ ጠጥቶ ከቤት ሲወጣ ከአጎቴ ቤት በር ላይ ያለው የቀጋ ዛፍ ጋቢውን ጥርቅም አድርጎ ያዘው። የቀጋው እሾህ ጋቢውን በያዘው ጊዜ ጋቢውን የያዘው አጎቴ መስሎት እባከህ ወዳጄ ልቀቀኝ ከዚህ በላይ አልጠጣም! ልቀቀኝ ልሂድበት እያለ ጋቢውን ሞጭጮ ከያዘበት የቀጋ ዛፍ ጋር ይሟገታል። የቀጋው ዛፍ ግኡዝ ስለሆነ አልመለሰም። አቶ ፈጠነም ቀጋው ጋቢውን አለቅ ስላለው የአጎቴን ስም እየተጣራ ጋቢውን ከአስቀረህ አስቀረው እንጂ ከዚህ በላይ አልጠጣም፣ በቅቶኛል ብሎ ጋቢውን ቀጋው ላይ ጥሎት ሄደ። እኔም በአቶ ፈጠነ እና በቀጋው ዛፍ መካከል የነበረውን ትዕይንት ለአጎቴ እና አጎቴ ቤት ተጠርተው ለመጡ እንግዶች ተናገርኩ።

አጎቴ እና ለማህበር ተጠርተው የመጡ ሰዎችም አቶ ፈጠነ ወዴየት እንደሄደ ጠየቁኝ። እኔም የሄደበትን አቅጣጫ አሳየሁ። ሰዎችም አቶ ፈጠነ የሄደበትን አቅጣጫ ተከትለው ቢሄዱ የሰፋራችን ሰዎች ውሃ ከሚቀዱበት ጅረት መሀል ተኝቶ ተገኘ። የማህበሩ ሰውም ሰውየው የሆነ ነገር ቢሆን ነገ እዳው ለእኛም ጭምር ይተርፋል በማለት ከወደቀበት ሊያነሱት ሞከሩ። አቶ ፈጠነም የተኛሁበት ተመችቶኛል ማንም ሰው እንዳይነካኝ!... አልነሳም! ብሎ እምቢ አለ። ሰው መጥፊያውን ይወዳል ማለት ይሄ አይደል !

የሰፈራችን እና የእድራችን መሪዎች እና ተፎካካሪዎች እንደ አቶ ፈጠነ ያለመጠን ያገኙትን እየበሉ እና እየጠጡ በጥጋብ ሰክረው በሰፈራችን ላይ ችግር መፍጠራቸው ሳያንስ፤ በእነሱ ችግር ሰፈራችንን እና እድራችንን ሊፈርስ መሆኑን የሚነግራቸው ሰው ሲመጣ እንኳን ለመስማት ፈቃደኛ አይደሉም። የሚጠየቁት ሌላ የሚመልሱት ሌላ .... አራምባ እና ቆቦ።

ይህን ስል ........

"ጥርስ የለውም እንጂ ይናከሳል ጉዳን፤

የፈረንሳይ ዋና ከተማ እንደምነሽ ሱዳን፤" የሚውን የተስፋየ ካሳ ቀልድ ያስታውሰኛል።

በመጨረሻም በአንድ ሃገር ሰላም ፤ መረጋገት እና እድገትን ለማምጣት ከተፈለገ ተገቢው ቦታ ለተገቢው ሰው መሰጠት አለበት የሚለውን የኮንፊሼስ አባባል ያለምንም ማንገራገር መዋጥ ያስፈልጋል ባይ ነኝ። አይደለም ሃገርን ይቅርና በአንድ ቤት ውስጥ እንኳን ሰላም እና እድገትን ለማምጣት ከተፈለገ ተገቢው ቦታ ለተገቢው ሰው መሰጠት ያስፈልጋል። የአባትን ቦታ ለልጅ ከሰጠን ልጅ የአባትን ያህል ቤቱን ሊመራ አይችልም። የቄስን ቦታ ለጨዋ ሰው ከሰጠንም እንዲሁ የቄሱን ያህል ቤተክርስቲያኗን ስርዓት እና ወግ ማከናወን አይችልም። ስለዚህ የሰፈራችንን እድር ሰላም እና እድገት ለማምጣት ተገቢውን ቦታ ለተገቢው ስጡ። መልዕክቴ ነው ! ብሎ ይልቃል አዲሴ ንግሩን ሲጨርስ ሊያጨበጭቡ የነበሩ ሰዎች መልሰው እጃቸውን ሰበሰቡ። የተነገራቸውንም እያወጡ እና እያወረዱ ወደ መጡበት ተመለሱ።

**በአንድ ሃገር ሰላም ፤ መረጋገት እና እድገትን ለማምጣት ከተፈለገ ተገቢው ቦታ ለተገቢው ሰው መሰጠት አለበት**

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# የዓባይ ዘመን ብዕር ትናንትና ዛሬ

**ዋስልኝ አየለ**



በእንጉርጉሮ ሲገለጽ የኖረው ዓባይ አሁን ደግሞ በህዳሴ ግድብ ግንባታ እየተገባደደ መምጣት ሀይል ወደ ማመንጨት መሸጋገሩን ብእሮች ይገልጹት ጀምረዋል

ዓባይ/ወንዙ/ በተለያየ ዘመን የተለያየ ስሜትን ይገልጻል። ጥንት ድልድይ ከመኖሩ በፊት በዓባይ ወንዝ ሳቢያ የተቆራረጡ የወዲያ ማዶ እና የወዲህ ማዶ ሰዎች በእንጉርጉሯቸው የሚናገሩት የዓባይን አስቸጋሪነት ነበር። ስለዚህ እነዚያ የጥንት የስነ ቃል ግጥሞች ዓባይ ምን ያህል ያስቸግር እንደነበር ይነግሩናል ማለት ነው።

ዛሬ ዓባይን ለመሻገር ያን ያህል ፈተና አይደለም። ድልድይ ተሰርቷል። ይህም በተለያዩ የጥበብ ሥራዎች ሲገለጽ ቆይቷል።

የአሁኑ የዓባይ ዘመን ጥበብ (ብዕር) ግን ይለያል። የአሁኑ የዓባይ ዘመን ብዕር ግንድ ይዞ ይዞር የነበረውን ዓባይ ማደሪያ ተዘጋጅቶለት ማደሪያው የታወቀውን ዓባይ የሚገልጽ ነው።

ከባለፈው ዓመት ጀምሮ ‹‹የዓባይ ዘመን ብዕር›› የተሰኙ በርካታ የኪነ ጥበብ መድረኮች ተዘጋጅተዋል። በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ሲካሄድ ቆይቷል። የዘንድሮውን ለየት የሚያደርገው ደግሞ ኃይል ማመንጨት የጀመረበት መሆኑ ነው። የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ 11ኛ ዓመት እና ኃይል ማመንጨት የጀመረበትን ወቅት ምክንያት በማድረግ በተለያዩ አካባቢዎች ሲከበር ቆይቶ ባሳለፍነው ሳምንት ሚያዚያ 7 ቀን 2014 ዓ.ም በአዲስ አበባ ግዮን ሆቴል የማጠቃለያ ፕሮራግሙ ተደርጓል።

ማጠቃለያ ፕሮግራሙ ላይ በብዛት የቀረቡት ግጥሞች ናቸው። በመጨረሻም ዓባይን የሚመለከት አጠር ያለ ቴአትር ቀርቧል። ስለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ስለዓባይ ሲከራከርና የኢትዮጵያን እውነታ ሲያሳውቅ የቆየው መሀመድ አል አሩሲ አጠር ያለ ንግግር አድርጓል።

ለማንኛውም የዛሬው ጽሑፋችን ዓላማ የመድረኩን ሁነት መዘገብ አይደለም፤ ማጠቃለያውን ምክንያት በማድረግ የዓባይ ዘመን ብዕሮችን መዳሰስ ነው።

በነገራችን ላይ ‹‹የዓባይ ዘመን ብዕር የተሰኘ መጽሐፍ በ2012 ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ ታትሟል። በመጽሐፉ 50 ወጣትና አንጋፋ ደራሲያን ተሳትፈውበታል። በወቅቱ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት እንደዘገበው፤ ‹‹የዓባይ ዘመን ብዕር›› ስለ ዓባይ የተነገሩ እንጉርጉሮዎች፣ ሀዘንና መፋዘዝን በተስፋ፣ በመጪው ጊዜ ትንበያና ጥልቅ ምርምር በሚሹ ስራዎች የተካ የግጥም መድበል ነው።

የኢትዮጵያ ፀጋ የሆነው ዓባይ ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ምንም ሳይፈይድ ዝንተ ዓለም ወደ ባእድ አገር መፍሰሱ ያስቆጫቸው ባለቅኔና ደራሲያን፤ ገጣሚያንና የጥበብ ሰዎች ቁጭት አዘል ስራዎቻቸውን በሙዚቃ፣ በሥነ-ፅሑፍ፣ በስዕል በመግለጽ ወደ ቤቱ የሚመለስበትን ዘመን ሲናፍቁ ኖረዋል። መጽሐፉ እነዚያንም ይጠቃቅሳል። የዓባይን የስልጣኔ፣ የሀብት፣ የኩራት፣ የውበት ምንጭነትና የአገር ቅርስነት በቁጭት ሲያወሱ ኖረዋል፤ በእዚህ መንገድ ዓባይ ተሞግሷል፣ ዓባይ እንደ ሰው ተወቅሷል፣ ዓባይ ተሰድቧል።

የዓባይን ታሪክ የቀየረውና ኢትዮጵያዊያን በአንድ ዓይን እንዲመለከቱ ያደረገው የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ጥበበኞቹንም ተስፋን የሰነቁ ስራዎች ይዘው እንዲወጡ ዕድል ሰጥቷቸዋል። እነዚህ ጥበበኞች ናቸው መጽሐፉን የጻፉት።

መጽሐፉ የተዘጋጀው በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ብሔራዊ ምክር ቤት ፅህፈት ቤት ነው። በውስጡም ዓባይን የተመለከቱ ወጥ ሥነ ግጥሞች፣ ወግና የዘፈን ግጥሞች ተካተውበታል፤ ኢትዮጵያውያን ቁጭታቸውን በብሩህ ተስፋ በማለምለም በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የድርሻቸውን እንዲወጡም ያሳስባል።

የስነ ጽሑፍ ባለሙያው ጸሐፊ ተውኔት አያልነህ ሙላት በአንድ ወቅት ስለዓባይና ኪነ ጥበብ በአንድ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ፕሮግራም ላይ እንደተናገሩት፤ ዓባይና ኪነ ጥበብ ለረዥም ዘመን አብረው የኖሩ ናቸው። እረኛው፣ አዝማሪው፣ አልቃሹ፣ አሚናው፣ ... ይሄ ሁሉ ስለዓባይ ሲናገር፣ ሲዘምር ነው የኖረው። ጥያቄው ምን ነበር ካልን፤ ይሄ ሁሉ ዘማሪ ሊሆን የቻለው የዓባይ ጥቅም ገብቶት ብቻ አይደለም። ይልቁንም እንደ ትልቅ ክብር ስለሚያየው ነው።

እንደ ጸሐፊ ተውኔቱ ገለጻ፤ ህብረተሰቡ እየተለወጠ፣ እየተማረና እያወቀ ሲመጣ ሁኔታዎችም ተለወጡ። ከምንጭነቱና ከኩራትነቱ አልፎ ጠቀሜታ የሚሰጥ መሆኑ፣ ከሌሎች አገሮችም ተሞክሮ እየታወቀ ሲመጣ፣ የዓባይ ዘመን ጥበብም አይነቱን እየለወጠ መጣ። አሁን እየተሰሩ ያሉ ግጥሞችም የዓባይን ጠቃሚነት የሚያጎሉ ናቸው። ተውኔቶቹም አገር በቀል መፍትሔ ላይ የሚያተኩሩና መተባበርን የሚያሳዩ ናቸው።

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የግንባታው ሀሳብ ከቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ጀምሮ እንደነበር ይነገራል። ያንን ተከትሎም ከያኒያንም ቁጭት ማሰማት ጀምረዋል። ከጥንት ስነ ቃል ወጥተው ገጣሚያን የራሳቸውን ቅኔ ተቀኝተውበታል። በተለይም የሎሬት ጸጋዬ ገብረመድኅን ተጠቃሽ ነው። ‹‹እሳት ወይ አበባ›› ከተሰኘው ከሎሬቱ መድብል ስለዓባይ ከገጠመው ረጅም ግጥም ቀንጭበን እንመልከት።

አባይ የምድረ ዓለም ሲሳይ
የቅድመ ጠቢባን አዋይ
አባይ የጥቁር ዘር ብስራት
የኢትዮጵያ ደም የኩሽ እናት
የዓለም ስልጣኔ ምስማክ
ከጣና በር እስከ ካርናክ
በእቅፍሽ ውስጥ እንዲላክ
በመመለክ በመመስገን
ጽላትሽ ከዘመን ዘመን
በአዝዕርትሽ አበቅቴሽ ሲታጠን
አቤት አባይ ላንቺ መገን።
አድርጎሽ ቅድመ ገናና
ዛሬ ወራቱ ራቀና
ምድረ ዓለም አድናቆት
ፈለጉን መሻት ተስኖት
እንዲህ ባንቺ መንከራተት
ታሪክ ወሮታሽ ጠፍቶበት
ትላንት በባዕድ ጩኸት
ዛሬም ባላዋቂ ሁከት
ቋንቋ ለቋንቋ ቢራራቅ
የቅድሚያሽ ንድፍ ላይፋቅ
እዚህ ደማም እዚያ ተማም
መበልሽ ብቻ ባይበቃም....

እያለ ዓባይንም ኢትዮጵያንም ይራቀቅባቸዋል። ዓባይን ያሞግሰዋል፤ ይወቅሰዋል። በእነ ሎሬት ጸጋዬ ጊዜ ገና ሀሳብ ላይ የነበረው ዓባይ ቁጭት ማጫር ጀምሮ ነበር። እነሆ የማይደፈር የሚመስለው ዓባይ ተደፍሮ መገደብ ሲጀመር ደግሞ የዘመኑ ከያኒያን ከቁጭት ወደ ተስፋ ተሸጋገሩ። የእነ ሎሬት ጸጋዬ ተከታይ የሆኑት እነ አርቲስት ጌትነት እንየው ዓባይን ከቁጭትነቱ ጀምረው እስከ ተስፋነቱ ገልጸውታል። እስኪ ይህን ወኔ ቀስቃሽ የጌትነት እንየው ግጥም እናንብብ!

በአገር ግፍ መዋሉን መበደሉን ትቶ
ባለፈ ተግባሩ በጎደፉ ስሙ አፍሮ ተጸጽቶ
በጊዜ ንስሃ ከዘመናት መርገምት ከበደሉ ነጽቶ
ከቆየ ልማዱ ከኖረ ምግባሩ ከባህሪው ወጥቶ
ውሃነቱን ትቶ
ወንዝነቱ ቀርቶ
እንዳንዳች ምትሀት ከቃልኪዳን ስሩ እየተመዘዘ
በአንድ የስሜት ግለት በአንድ የስሜት ሲቃ
አገር ጫፍ እስከ ጫፍ ሰቅዞ እየያዘ
ትውልድን ከታሪክ ታሪክን ከአገር ስቦ እያዋደደ
አስማምቶ እያሰረ
ስሩ የጠለቀ
ግብሩ የረቀቀ
ውሉ የጠበቀ አባይ ሀረግ ሆነ ከደም የወፈረ
ይሄው ከዓይናችን ስር ዘመን መሰከረ
ይሄው ከእጃችን ላይ ግዮን ተቀየረ...
ከእንግዲህ ባገሩ ሳቅ እና መስኖ እንጅ እንባ ሆኖ
ላይገርፍ
ከእንግዲህ ላገሩ እጁ ላይታጠፍ
ጸጋው ላይገፍ
ግቱም ከቶ ላይነጥፍ
ከእንግዲህ ፍቅር እንጅ ሽፍጥ እና ድለላ ስሩን
ላያስረሱት
ከእንግዲህ ምክር እንጅ ብረት እና ሴራ ውሉን
ላያስረሱት
ያገር ውርስ እና ቅርስ እራት እና መብራት
ዋስ ጠበቃ ሊሆን መከታ እና ኩራት
የአገር ውርስና ቅርስ ራትና መብራት፣
ዋስ ጠበቃ ሊሆን ክብርና ኩራት፣
ይኸው በአዲስ ዘመን አዲስ ቃል ዘመረ፣
ከራሱ ታረቀ ካፈሩ መከረ፣
ለአገሩ ቆመ በአገሩ አደረ፣
ዜማና ቅኝቱ ረገደ ምቱ፣
ከጊዜ ከትውልድ ከሀቅ ሰመረ፣
ሃገርን ባንድ ነዶ ባንድ ልብ አሰረ
ይኸው ካይናችን ስር ከእውነት የነጠረ ከእምነት
የጠጠረ፣
አባይ ሃረግ ሆነ ከደም የወፈረ።
የአንድ ወንዝ ልጅ ሁሉ ይህን የአባይ ሀረግ
ከእምነትህ ጋር ቋጥረህ
ከጋራ አንገት መድፋት ከጋራ መሳቀቅ ከጋራ አፍረት
ወጥተህ
በያለህበቱ በየዓለማቱ ጥግ በአንተነትህ ኮርተህ
አንተ ማነህ ሲሉህ
ከወዴት ነህ ሲሉህ
በሙሉ ራስነት አንገትህ አቅንተህ
ድምጽህን ከፍ አድርገህ
ደረትህን ነፍተህ
የአባይ ልጅ ነኝ እኔ
ጦቢያ ናት አገሬ በል አፍህን ሞልተህ!

የአንጋፋዎቹ ገጣሚዎች ስራዎች ብቻ አልነበሩም በየመድረኩ ይቀርቡ የነበሩት። የተለያዩ መድረኮች እየተዘጋጁ ግጥሞች ሲቀርቡ ቆይተዋል። ባለፉት 11 ዓመታት ዓባይን በተመለከተ በመድረክ የሚቀርቡ ግጥሞች ሁሉ የህዳሴ ግድቡን ተስፋ ሰጪነት የሚጠቁሙ ናቸው። ቁጭት ሳይሆን፤ ተስፋ፣ ወኔ እና የአሸናፊነት መልዕክት ያላቸው ናቸው። በእረኞችና ገበሬዎች ተወስኖ የነበረው የዓባይ እንጉርጉሮ ከተማሪ እስከ ተመራማሪ ድረስ ተቀኙበት። መድረኮች ተዘጋጅተውለት ተወደሰ።

በጽሑፋችን መግቢያ አካባቢ ስለጸሐፊ ተውኔት አያልነህ ሙላት ካነሳሁት አንድ ሀሳብ ቀንጭቤ ነበር። እረኛው፣ አዝማሪው፣ ገበሬው... ስለዓባይ ሲያንጎራጉር ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ይገደባል ብሎ አይደለም። እንዲያውም እረኛ ከውሃ የኤሌክትሪክ ኃይል እንደሚገኝም ላያውቅ ይችላል። እሱ የሚያንጎራጉረው ዓባይ ማንነቱና ኩራቱ ስለሆነ ነው። ዓባይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማንነት ስለሆነ ነው። ክረምት ከበጋ ከዓባይ ጋር የሚያገናኘው ብዙ ማህበራዊ ሕይወት ስላለው ነው። ዓባይ ከወንዞች ሁሉ የተለየ ግዙፍ መሆኑ አንዳች ግርምት ስለሚፈጥርበት ነው።

ግብጾች ስለዓባይ ምን እንደሚሉ በምሁራን ሲተነተን ቆይቷል። ‹‹ደምና አጥንታችን ነው›› ይላሉ። ዓባይ ማንነታቸው እንደሆነ እና ለኢትዮጵያ ግን የቅንጦት መስሎ ነው የሚታያቸው። ዳሩ ግን ዓባይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማንነት መሆኑን የጥንት የሕዝብ ስነ ቃል እና የኪነ ጥበብ ሥራዎችም ሲመሰክሩ ኖረዋል። ታላቅነት፣ ለጋስነት፣ አይበገሬነት፣ ተጓዥነት... በዓባይ ይመሰላሉ። ተረቶች ዓባይን መነሻ ያደርጋሉ። ለዚህም ነው ዓባይ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ጥንታዊ ትስስር ያለው መሆኑ ሁሌም የሚገለጸው።

‹‹የዓባይ ዘመን ጥበብ›› ገላጭ የሆነ ሀሳብ ነው። የጥንቱንም የዛሬውንም ምንነቱን የሚገልጽ። በተሳተፍኩባቸው የዓባይ ዘመን ጥበብ መድረኮችም ሆነ በመገናኛ ብዙኃን በተከታተልኩት የጥበብ ሥራዎች የዓባይን የጥንቱን መነሻ አድርገው የአሁኑን ይገልጻሉ። ቀጣይ ለሚመጣው ትውልድ ደግሞ የዛሬ የጥበብ ሥራዎች በዚህኛው ዘመን ያለውን ዓባይ የሚገልጹ ናቸው። ቀጣይ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ መደበኛ አገልግሎት እየሰጠ፣ ብርቅ መሆኑ ተለምዶ፣ ኢትዮጵያም ያሰበችው ብልጽግና ላይ ደርሳ ለማየት ያበቃው ትውልድ፤ በግድቡ ተሳትፎ ጊዜ ምን ይባል እንደነበር እነዚህ የጥበብ ሥራዎች ይመሰክራሉ።

ስለዚህ የዓባይ ዘመን ጥበብ፤ ትናንትም፣ ዛሬም ነገም ነውና ከያኒያን መጠበባቸውን ይቀጥሉ!

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ያለንበት ሁኔታ

**ግርማ መንግሥቴ**

ያለንበት ሁኔታ የሚታይ፣ የሚዳሰስ፣ የሚሰማ .... ነው። ችግርም አለ፤ ደስታም አለ። ሁለቱንም እያስተናገድን ሲሆን፤ በተለይ "ችግር" ሆኖ እያስቸገረን ላለው ምክንያቶቹ፣ መነሻዎቹ፣ ምንጮቹ እኛው ሆነን ነው የምንገኘው።

ያለንበት ወቅት፣ በተለይ ሁለቱ በርካታ ምእመናን ያሏቸው ኃይማኖቶች ተከታዮች ሁለቱም በየራሳቸው ፆም (ሁዳዴ እና ሮመዳን) ላይ ያሉበትና ኃይማኖታዊ ስርአታቸው በሚፈቅደው (በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው) መሰረት፤ ከፆምና ፀሎት ባሻገር፣ ሰብዓዊ ተግባራትን በማከናወን ላይ ናቸው። ይህ በበርካታ አገራት የሌለ፤ ነገር ግን በኢትዮጵያ ሁሌም ያለ፤ በአግባቡ ከተያዘ የቱባ ባህላችንና እሴቶቻችን አካል በመሆን በማንኛውም መልኩ ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳ ያለው ነው።

ያለንበት ሁኔታ በአላትን ለማክበር፤ ፆም ፍቺን ለመያዝ በከፍተኛ ደረጃ ሽር ጉድ የምንልበት፤ የደራ ገበያን የምናስተናግድበት፤ ኢኮኖሚያዊ አቅማችን በከፍተኛ ሁኔታ የሚፈተንበት፤ እንኳን አደረሰን፣ አደረሳችሁ ለመባባል ቀናት እየቀሩን ነው። እነዚህና ሌሎች ሁሉ ይሁን እንጂ እነዚህን ሁሉ የሚያደበዝዝ ሁኔታ ደግሞ አለ - ገበያው።

ያለንበት የገበያ ሁኔታ የሰከረ የሚመስል፤ ሰክሮም ሰውንም የሚያሰክር የሚመስልበት ነው። ሁኔታው ሁሉ ለያዥ ለገናዥ ያስቸገረ ሁሉ ይመስላል። የትናንት ዋጋ ዛሬ የለም፤ የዛሬ ዋጋ ነገ የለም። ገበያው "አበደ" ሲሉት አፍታም ሳይቆይ ወደ "ከነፈ" ይሸጋገራል። ሲበዛ እየጨከነ፤ በጣም ሲበዛም ርህራሄ የለሽ እየሆነ ሰውን ሁሉ ከለመደው፣ ከባህሉና ከዓመት በዓሉ አውድ ሊነጥለው ሁሉ እየዳዳው ይገኛል።

ገበያው ለማበዱ መገለጫው ብዙ ሲሆን አንዱና ዋናው ግን ደላላ መር የገበያ ሁኔታ መኖሩ ነው። ነጋዴው ነገ ለማስወደድ ሲፈልግ ዛሬ ደላላውን ያስፏጨዋል፤ "ፍየል 40ሺህ ብር ገባ" ያስብለዋል፤ "በሬ 100ሺህ ..." ይል ዘንድ ያስምለዋል። ሲሚንቶ ....፤ ጤፍ ..... ዘይት ....፣ በቃ ... ገበያው ይህ ሆኖ ካረፈው ቆየ። ሃይ ባይ ከጠፋ ሰነበተ። በሻጭ ነጋዴው ዘንድ እፍረት ከኮበለለ፣ አገራዊም ይሁን ሙያዊ ሀላፊነት ጨርቁን ከጣለ፤ ይሉኝታ ኮፍያውን ካወለቀ፤ ከመተሳሰብ ተርታ ከወጣ ... ወቅቱ አሁን ሳይሆን ከርሟል። እንደ ነጋዴው ቢሆን ኖሮ ነባሩ የመተሳሰብ፣ የመተጋገዝ ... ኢትዮጵያዊ እሴት ጓዙን ጠቅልሎ ገና ድሮ በጠፋ ነበር። ግን ለህሊናቸው ባደሩት ኃይላት እነሆ እስካሁን አለን እንጂ እንደ አንዳንዶችማ ብን ብለን በተነንን ነበር።

በዚሁ ጉዳይ ላይ ይህ ጸሐፊ ያነጋገራቸው የከተማዋ ነዋሪዎች ያሉ ሲሆን የሁሉም ድምፅ ተመሳሳይ ሲሆን፤ ይጠቃለል ከተባለም ተስፋ የመቁረጥ፤ የሚያሳዝንና የተማፅኖ የሚመስል ነው።

ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ፣ በተለይም ከወቅታዊው የገበያ ይዞታ አኳያ ያለውን አስተያየት እንዲያካፍለን የጠየቅነው የባንክ ባለሙያው አብረሃም ማርቆስን ነው። ወጣት አብረሃም በጉዳዩ ላይ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ጋር የቅርብ ግንኙነት እንዳለው ባለሙያ ሆኖ አይደለም ሲያነጋግረን የነበረው። አብረሃም ለጥያቄያችን መልስ ሲሰጥ የነበረው ሙያውን ተንተርሶ ሳይሆን ወደ ማህበራዊነት ባደላ መልኩ ነበር።

ለአብረሃም "ስለ ገበያው ሁኔታ ምን አስተያየት አለህ?" ስንል ላቀረብንለት ጥያቄ ገራገር በሆነ መልኩ "ምናለ ብንተሳሰብ፤ ምናለ ብንደጋገፍ፤ ለምን አንዱ በከፍተኛ ደረጃ ሲያከብር ለምን ሌላው ከዛ ውጭ እንዲሆን ይደረጋል? እኔ ይሄ ነው ይሄ ነው የምለው ነገር የለም፤ ለምን አንተሳሰብም? ካልተሳሰብን እኮ እንደ ሰው መኖር አንችልም። መተሳሰብ የግድ ያስፈልገናል። ያለውም የሌላውን እንድያስብ ጭምር።" በማለት ነበር የመለሰልን። ሰፋ ባለ መልኩ በጉዳዩ ላይ የተነጋገርን ቢሆንም አጠቃላይ ሀሳቡ የመተሳሰብ አስፈላጊነት፤ ያልተፈለገ ትርፍ መሻት አላስፈላጊነት ላይ ያተኮረ ነበር። ሕግን የሚፈራ፣ ሀይ ባይ በታጣበት ቦታና ሁኔታ ... የአብረሃም "እንተሳሰብ፣ አስቡልን ..." አስተያየት ልክ ሳይሆን አይቀርምና የሚሰማ ካለ "እባካችሁ እንተሳሰብ፤ ቀድማችሁ አውዳመታችንን አትንጠቁን፤ ፍየል 40ሺህ .... ምናምን አትበሉን" ቢባል ያስኬዳል።

አብረሃም "ለመላው ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች እንኳን አደረሳችሁ!!!" ከሚለው ሌላ፤ ለሕዝቡም፣ ለሸማቹም የሚያስተላልፈው መልእክት አለው፤ ሕዝቡ ህገ ወጥ ንግድን በማጋለጥ ከመንግስት ጎን እንዲቆም፤ ሸማቹም ለአመት በአል ብሎ የህገ ወጥ ነጋዴዎች ሰለባ እንዳይሆን ይመክራል።

ሌላው ያነጋገርነው የፈረንሳይ አካባቢ ነዋሪ፣ በግል ስራ የሚተዳደረው፣ መልእክቱንም "በዓሉ የሰላም፣ የመተሳሰብ፣ የፍቅርና አብሮነት ይሁንልን!!!" በማለት የደመደመው አቶ ሸዋንዳኝ ታደሰ ነው። እንደ አቶ ሸዋንዳኝ አስተያየት መንግስት በህገወጥ ነጋዴዎች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል። ሸማቹም ለአንድ ቀን ዓመት በዓል ብሎ ለህገ ወጥ ንግድ መጋለጥ፤ ተጠቂ መሆን የለበትም። መንግስትም እንደ ሸማቾች አይነቶችን በስፋት በማደራጀት ለሕዝቡ ምርቱን ተደራሽ ማድረግ አለበት።

ሌላው ያለንበት ሁኔታ የሰላምና ፀጥታው ጉዳይ ነው። ይህንን ጉዳይ እየተካሄደ ወዳለው የእርስ በእርስ ግጭት አልወስደውም። ከዛ በመለስ ያለውንና በተለይ ከትንሽ እስከ ትልቅ ከተሞቻችን ድረስ የነዋሪዎች ራስ ምታት የሆነውን ወጥቶ የመግባትና ያለ ስጋት የመንቀሳቀስ ጉዳይ ነው የማነሳው። በተለይም በተለምዶ "ጫኝ" እና "አውራጅ" ከሚባለው ስራና ሰራተኞቹ ከሚባሉት አኳያ ከተሞቻችን ምን ይመስላሉ የሚለውን ቆም ብሎ ላገናዘበ የሚደርስበት ድምዳሜ ቢኖር ያለንበት ሁኔታ የሕግ ሳይሆን የጉልበተኞች የበላይነት የተንሰራፋበት መሆኑን ነው።

ዛሬ በከተሞች የፌስታል እቃ እንኳን ባለ ፌስታሉ ከታክሲ ላይ ማውረድ አይችልም። ይህንን የማድረግ ምንም አይነት መብት የለውም። ባለቤቱ እኔ ነኝ፤ በሕግ አምላክ .... የሚሉት ከምንም የሚያድኑ አይደሉም። እቃዎትን አንድ ገረምሳ (ወይም የጎረምሶች ቡድን) ምጥቶ ያወርደዋል። የፈለገውን ያህል ብር አምጣ/ጪ ይላል። ይወስዳል። ይህንን አልፈፅምም ካለ የባሰ እንጂ ሌላ የሚያተርፈው ነገር የለምና መክፈሉ "አማራጭ የሌለው መፍትሄ?" ይሆናል (ወደ ፖሊስ ቢኬድ "ተስማሙ")።

በከተሞቻችን በሞተር እየሄዱ ንብረት መንጠቅ፣ ቁልፍ የሆኑ መንገዶች ላይ ተሰብስቦ በመቀመጥ ገበያተኛ ገዝቶ ሲወጣ ገንዘብ አምጣ (ክፈል) ማለት፤ አልሰጥም ካለ ወደ ማስገደድ መሄድ .... የተለመዱና የከተማ ነዋሪዎች የእለት ተእለት ሕይወት አካል እየሆኑ ነው።

ያለንበት ሁኔታ የፖለቲካ ንቁሪያ የበዛበት፣ የመግባባት ሚዛኑ ወደ አለመግባባት ያጋደለበትና ሰርክ ጭቅጭቅ የሆነበት ነው። ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ፖለቲካ መስማት የማይፈልግ፣ በተለይም የብሄር ፖለቲካ በደረሰበት መድረስ የማይፈልግ ሰው የሚኖርባት አገር አልመስል እያለች ነው። አስቀድሞ ሁሉ አዋቂ፣ ሁሉ ተቺ ... እንደ ተባለው የነሸጠው ሁሉ እየመጣ የአገሪቱን ፖለቲካ በዘር ከረጢት ውስጥ ከትቼ ያሻኝን ካላደረኩ ባይ ነው። የሰላም፣ እድገትና አብሮነት አማራጭ ሀሳብ ይዞ የመምጣት ምንም አይነት እቅድ የሌለው ፖለቲከኛ ቁጥሩ እየጨመረ ሲሄድ እንጂ ሲቀንስ አይስተዋልም። ባጭሩ፣ ፖለቲካችን ወከባ እንጂ ሌላ ጠብ እሚል ነገር እያጠጠው ይገኛል።

ያለንበት ሁኔታ የምዕራቡ ዓለም እንደ ፈለግሁ ካላደረኳችሁ እያለ ሌት ተቀን እያስፈራራን የሚገኝበት ነው። አሜሪካና ተባባሪዎቿ እነ ኤችኤር 6600ን በመሳሰሉ የማእቀብ ጋጋታዎች እጃችንን ለመጠምዘዝ እየጣሩ ነው። ይህ ጊዜ ከምን ጊዜውም በላይ አንድ ልንሆን የሚገባን ጊዜ ሆኖ ሳለ፤ አንድ እንዳንሆን፣ ሆነንም ጥቃትን እንዳንከላከል እኛኑ እየሸነሸኑ እርስ በርሳችን በማናከስ የሚፈልጉትን ለማድረግ እየጣሩ ያሉበት ወቅት ነው።

በአጠቃላይ ያለንበት ሁኔታ መልኩ ብዙ ነው። ይሁን እንጂ መፍትሄው ግን አንድ ነው - አንድ መሆን፤ ከላይ ያነጋገርናቸው አብረሃምና ሸዋንዳኝ እንዳሉት መተሳሰብ፤ መደጋገፍ ... ነውና እሱው ላይ እንበርታ።

**መልካም በዓል!!!**

# ዓለም አቀፍ

## የሱዳን ተቃዋሚዎች በተመድ እና በአፍሪካ ህብረት የቀረበውን የ"እናደራድራችሁ' ጥያቄ ሳይቀበሉ ቀሩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የሱዳን ተቃዋሚዎች በተባበሩት መንግስታት ድርጅት እና በአፍሪካ ህብረት የቀረበላቸውን የየ'እናደራድራችሁ' ጥያቄ ሳይቀበሉ ቀሩ።

ተቃዋሚዎቹ ከድርድሩ በፊት ሊተገበሩ ይገባል ያሏቸውን ቅድመ ሁኔታዎች አስቀምጠዋል።

ከቅደመ ሁኔታዎቹ አንዱ በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አብደላ ሃምዶክ ይመራ የነበረውን የሲቪሊያን አስተዳደር ከሽግግር መንግስቱ አስወግዶ ስልጣን የያዘው የአገሪቱ ጦር ስልጣኑን ያስረክብ የሚል ነው።

በሌ/ጄ አብዱል ፈታህ አል ቡርሃን የሚመራው የአገሪቱ ጦር ባሳለፍነው ወርሃ ጥቅምት መጨረሻ "የእርምት ነው" በሚል በወሰደው እርምጃ የሃምዶክን አስተዳደር በአዲስ መተካቱ ይታወሳል።

"በምርጫ ካልሆነ በስተቀር ስልጣን አሳልፈን አንሰጥም"- የሱዳን ጦር መሪ

ይህን ተከትሎ ሱዳናውያን ወደ አደባባዮች በመውጣት ተቃውሟቸውን ሲገልጹም ነበረ። ተቃውሞውን ተከትሎም ሱዳን በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ውስጥ ለመቆየት ተገዳለች።

በተለያዩ ጊዜያት የተካሄዱ ተቃውሞዎችን ተከትሎ በተቀሰቀሱ ግጭቶች 90 ሱዳናውያን ሲሞቱ 3 ሺ ገደማ መጎዳታቸውም ተነግሯል።

በአገሪቱ ሙሉ የሲቪሊያን መንግስት ነው ሊመሰረት የሚገባው ያሉት ተቃዋሚዎች የቡርሃን ወታደራዊ መንግስት የጣለውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲያነሳም ጠይቀዋል።

ቡርሃን ወታደራዊ እርምጃውን ተከትሎ የታሰሩ ፖለቲከኞችን እንደሚፈቱ ከሰሞኑ መናገራቸው



ይታወሳል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በልዩ መልዕክተኛው ቮከር ፐርዝስ በኩል የሱዳን ኃይሎች እንዲቀራረቡ ለማድረግ የተለያዩ ጥረቶችን እያደረገ እንደሚገኝ ከአሁን ቀደም አስታውቋል።

ሆኖም ሱዳን ልዩ መልዕክተኛው ቮከር ፐርዝስ በራሴ ውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እየገቡ ነው ስትል ደጋግማ ከሳለች። ከአገሯ ልታባርራቸው እንደምትችልም ነው ስታሳስብ የነበረችው።

የአገሪቱ ሉዓላዊ የሽግግር ምክር ቤት መሪ አብዱል ፈታህ አል ቡርሃን በዚሁ ጉዳይ ላይ ልዩ መልዕክተኛውን አነጋግረው እንደነበር ይታወሳል።



## ጣሊያን በሩሲያ ላይ ካላት የነዳጅ ጥገኝነት ለመላቀቅ አፍሪካን እየተመለከተች ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ጣሊያን በሩሲያ ላይ ካላት የነዳጅ ጥገኝነት ለመላቀቅ አፍሪካን ተስፋ አድርጋለች ተባለ፡፡

የአገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት የአፍሪካን የነዳጅ አቅም በማማተር ላይ መሆናቸው ተነግሯል፡፡

ምዕራባውያን የሩሲያ ነዳጅ ላይ ማዕቀብ ከጣሉ በዓለም ገበያ ላይ ያልተጠበቀ አደጋ ያስከትላል ስትል ሩሲያ አስጠነቀቀች

አስቸኳይ የነዳጅ ገበያን ያገኙ ዘንድ ሚኒስትሮቿን ወደ ማዕከላዊ አፍሪካ መላኳም ነው የተነገረው፡፡ አንጎላ እና ኮንጎ ሪፐብሊክን በነዳጅ ግብይት አማራጭ አጋር ለማድረግ ስለማሰቧም ተሰምቷል፡፡

ጣሊያን 45 በመቶ ያህል የነዳጅ ፍላጎቷን የምታሟላው ከሩሲያ ነው፡፡ ይህም በሩሲያ ነዳጅ ላይ ጥገኛ ከሆኑ ጀርመንን መሰል የአውሮፓ አገራት አንዷ አድርጓታል፡፡ በዩክሬን ጦርነት ጉዳይ የራሷን አቋም ለማራመድ እንዳላስቻላትም ነው የተነገረው፡፡


አሁን ግን ከሩሲያ ጥገኝነት ለመላቀቅ አጥብቃ ትፈልጋለች፡፡ ምጣኔ ሃብታዊ ጥገኝነት ለፖለቲካ መጠቀሚያ መሆን አይገባውም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ማሪዮ ድራጊ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዲ ማዮ የተመራ ልዑክ ወደ ማዕከላዊ አፍሪካ ልከዋል፡፡

የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ነዳጅ ፍለጋ የገልፍ አገራትን መዞር ጀመሩ

ጣሊያን ከአሁን ቀደምም ተጨማሪ ነዳጅን እንድታቀርብላት ከአልጄሪያ እንዲሁም ከግብጽ ጋር ስምምነት አድርጋለች፡፡ ከሩሲያ በመቀጠል ለጣሊያን ከፍተኛ ነዳጅን የምታቀርበው አልጄሪያ ናት፡፡ 30 በመቶ ያህል ፍጆታዋን የምትሸፍነውም አልጄሪያ ነች፡፡

45 በመቶ ያህሉ የጣሊያን የኢነርጂ ፍጆታ በነዳጅ የሚሸፈን ነው፡፡ 95 በመቶ ያህሉ የነዳጅ አቅርቦትም ከውጭ የሚገባ ነው፡፡

# ስፖርት





## የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ የምድብ ድልድል

**ብርሃን ፈይሳ**

ኮትዲቯር አዘጋጅ የሆነችበት 34ኛው የአፍሪካ ዋንጫ የማጣሪያ ምድብ ድልድልን ካፍ ይፋ አድርጓል። በዚህም መሰረት ኢትዮጵያ በምድብ አራት ከግብጽ፣ ማላዊ እና ጊኒ ጋር መደልደሏ ታውቋል።

የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) በበላይነት የሚመራው የአህጉሪቷ ታላቅ የእግር ኳስ ውድድር በመጪው ዓመት በኮትዲቯር አዘጋጅነት እንደሚካሄድ ይታወቃል። በየሁለት ዓመቱ የሚካሄደው የአፍሪካ ዋንጫ እአአ በ2019 ካሜሮን፣ 2021 ኮትዲቯር እንዲሁም በ2023 ጊኒ አዘጋጅ በመሆን ተደልድለው ነበር፤ ይሁንና በመላው ዓለም በተከሰተው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት የውድድር መርሃ ግብሩ በመሸጋሸጉ ካሜሮን ከወራት በፊት ውድድሩን ማስተናገዷ አይዘነጋም።

በመሆኑም ኮትዲቯር በቀጣዩ የፈረንጆቹ ዓመት ለ34ኛ ጊዜ የሚካሄደውን የአፍሪካ ዋንጫ ታስተናግዳለች። በዚህ ውድድር ላይ ተሳታፊ የሚሆኑ ብሄራዊ ቡድኖችን ለመለየት የሚያስችለው የማጣሪያ ጨዋታ የምድብ ድልድልም ከትናንት በስቲያ ተካሂዷል።

በደቡብ አፍሪካዋ ጆሃንስበርግ በተካሄደው የእጣ ማውጣት ስነስርዓት ላይም 48 የካፍ አባል አገራት በ12 ምድብ ተደልድለዋል። እያንዳንዱ ምድብ አራት አገራትን የሚያቅፍ ሲሆን፤ በፊፋ እግድ የተጣለባቸው ኬንያ እና ዚምቧቡዌም (ማጣሪያው ከመጀመሩ ሳምንታትን አስቀድሞ ከእገዳ ነጻ ስለሚሆኑ ) በድልድሉ የተካተቱ አገራት ሊሆኑ ችለዋል።

ኢትዮጵያም በምድብ አራት፤ ከግብጽ፣ ማላዊ እና ጊኒ ጋር መደልደሏ ታውቋል። የሰባት ጊዜ የአፍሪካ ዋንጫ




ባለቤቷ ግብጽ በሴኔጋል ተሸንፋ ዋንጫውን ከማጣቷ ባለፈ ከኳታሩ የዓለም ዋንጫም በተመሳሳይ በሴኔጋል በደረሰባት ሽንፈት ከውድድር ውጭ መሆኗን ማረጋገጧ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ጊኒ እና ማላዊ በካሜሩን በተካሄደው የዓለም ዋንጫ ከዚህ ቀደም ከሚታወቁበት አቋም በተሻለ ሁኔታ የተገኙ ሲሆን፤ ምርጥ 16 ውስጥ መግባታቸው ይታወሳል። በአንጻሩ ከስምንት ዓመታት በኋላ ወደ አፍሪካ ዋንጫው የተመለሰችው ኢትዮጵያ ከምድቧ ማለፍ አለመቻሏ ይታወሳል።

የ33ኛው አፍሪካ ዋንጫ ባለቤት የሆነችው ሴኔጋል በመጨረሻው ምድብ 12፤ ከቤኒን፣ ሞዛምቢክ እና ርዋንዳ ጋር ተደልድላለች። የውድድሩ አዘጋጅ አገር ኮትዲቯር በበኩሏ በምድብ ስምንት ከዛምቢያ፣ ኮሞሮስ እና ሌሴቶ ጋር የምትጫወት ይሆናል። ኮትዲቭዋር ለአፍሪካ ዋንጫ ጨዋታው በቀጥታ የምታልፍ ሲሆን፣ ከተቀሩት አገሮች ጥሩ ውጤት ያገኘው ለአፍሪካ ዋንጫው የሚያልፍ ይሆናል። ምድብ 11 ጠንካራ ተፎካካሪዎች ያሉበት ሲሆን፤ ደቡብ አፍሪካ ከሞሮኮ፣ ዚምቧቡዌ ከላይቤሪያ ጋር ይገናኛሉ።

በአፍሪካ ዋንጫው ላይ ከ12ቱ ምድቦች አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃን ይዘው የሚያጠናቅቁ ብሔራዊ ቡድኖች የአፍሪካ ዋንጫን ተቀላቅለው በኮትዲቯር የዋንጫ ፍልሚያቸውን ያደርጋሉ። የማጣሪያ ውድድሩም በተያዘው መርሃ ግብር መሰረት በመጪው ግንቦት 2014ዓ.ም ላይ እንደሚጀመርም ታውቋል።

ኮትዲቯር እአአ በ1992 እና 2015 የአፍሪካ ዋንጫ ባለቤት ስትሆን፤ ለበርካታ ጊዜያት ደግሞ ወደ ዋንጫው ተቃርባ እንደነበር ይታወቃል። አገሪቷ እአአ በ1984 ይህንን ውድድር ካዘጋጀች በኋላም በቀጣዩ ዓመት ለሁለተኛ ጊዜ የምታስተናግደው ይህ የአፍሪካ ዋንጫ 24 አገራትን የሚያሳትፍ ይሆናል። ለዚህም አገሪቷ ስድስት ስታዲየሞችን እያሰናዳች ሲሆን፤ 40ሺ፣ 20 እና 15ሺ ሰዎችን መያዝ የሚችሉ የሁለት ሁለት ስታዲየሞች ዝግጅትም ይደረጋል።

በስታዲየሞቿ ብቁ አለመሆን ምክንያት የትኛውንም አህጉራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ ጨዋታ በአገሯ እንዳታስተናግድ የታገደችው ኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ በተሰጧት ግብረ መልሶች ላይ ማሻሻያ አድርጋ አላሳወቀችም። በዚህም ምክንያት ማጣሪያው የት ሊካሄድ ይችላል የሚለው የስፖርት ቤተሰቡ ጥያቄ ሆኗል። እንደ ከዚህ ቀደሙ በሌሎች አገራት ሜዳዎች ላይ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማውጣት ጨዋታ ከማድረግ ባለፈ በደጋፊ ፊት ከመጫወት ጋር ተያይዞ የሚገኘው ጥቅም በማጣት ውጤታማነቱ ላይ ተጽእኖ እንዳይፈጠርም ስጋት አሳድሯል።

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ሰኪና ሸምሱ መህዲ የሰሌዳ ቁጥር አአ 01-01-32633 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር JT1EOAE800003501l ሞዴል CORROLA (AE80) የሞተር ቁጥር 2A-5055324 የሊብሬ ቁጥር 460758 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 5/8/2014 አመልክተዋል፡፡ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ማክሲሚሊያን አለማየሁ ኢተፋ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A68855 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር JTFWS796400011353 ሞዴል KDN170L-CRMSYW የሞተር ቁጥር 2KD-1129538 የሊብሬ ቁጥር 419259 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 5/8/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረትስምግርማይትዕዛዙኀይለየሰሌዳቁጥርኢት03-01-98496የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5ELND3HD250793 ሞዴል ZZ3257N3647A የሞተር ቁጥር WD615.69*170807012797 የሊብሬ ቁጥር 0239771 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 5/8/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የየካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ፈቀደ ሙላት ወርቄ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-95096 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ-5BLSF7HN207017 ሞዴል ZZ1257S4341W የሞተር ቁጥር WD61.47*170417001457* የሊብሬ ቁጥር 0174825/0246725 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 5/8/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ይበሉ ሞሴዋ ይማም የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-23246 የተሽከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር TT1400-14 ሞዴል MIE/36H/FTL/3/7.5 የሞተር ቁጥር Trailer የሊብሬ ቁጥር 0127880 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 5/8/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አብይ ንጉሴ መኮንን የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-B00439 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር JT132LNB80 9020862 ሞዴል LN110L-CRMDSW የሞተር ቁጥር 2L-3939602 የሊብሬ ቁጥር 542033 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 3/8/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የየካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አስፋው ሌዳሞ ቢክሶ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A72146 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JAAN-PR71HK7100637 ሞዴል NPR6SN የሞተር ቁጥር 4HG1-765751 የሊብሬ ቁጥር 099030 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 3/8/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ቦሰና ገበየሁ ለገሰ የሰሌዳ ቁጥር አአ 01-01 30678 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር JT1L0EE8005075076 ሞዴል EE80L-ELMDCG የሞተር ቁጥር 2E-0662041 የሊብሬ ቁጥር 102190 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 4/8/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአራዳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ያርድስቲክ ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B35981 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር MALAF51CJNM167040 ሞዴል ATOS የሞተር ቁጥር G4HGMM112988 የሊብሬ ቁጥር 416629 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 30/7/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የየካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አድማሱ ጉሬ ወልደአብ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-09999 የተሽከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር CT1407-06 ሞዴል MIE36W-CT የሞተር ቁጥር Trailer የሊብሬ ቁጥር 0036213 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 5/8/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ኤርሚያስ እሸቱ ከበደ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-23457 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር W0B203046-1F-558577 ሞዴል C180 የሞተር ቁጥር 271946-30-356920 የሊብሬ ቁጥር 364977 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 4/8/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ጥበቡ ንጉሴ ስንቄ የሰሌዳ ቁጥር አአ 01-01-21854 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር STB-84078 ሞዴል 1300 የሞተር ቁጥር TC-74391 የሊብሬ ቁጥር 172236/570196 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 3/8/2014 አመልክተዋል፡፡የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ው ስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**